
# ፍኖተ ሕይወት

## ደራሲ፤ ሣህለ ሥላሴ ብርሃነ ማርያም

## ቅኝት፤ መስፍን ማሞ ተሰማ

__መንደርደሪያ__




ሥነ ፅሁፍ የሀገር ታሪክ ባህልና የህብረተሰብ ህይወት...በቃላት ደርዝ ተደርዘው ላለውና ለሚመጣው ትውልድ የሥነ ፅሁፍ ጠቢባን የሚያበረክቱት ቅርስ ነው። ጥበብ ነው ሥነ ፅሁፍ፤ የህቅ መልህቅ። ጥበብን ያላሸተ፤ እውነትንና ፍትህን ያላማጠ፤ ያልወለደ ሥነ ፅሁፍ - ምን ቢኳኳል ቃል በቃል፤ ምን ቢቀማጠል፤ ቢያማልል - እንኳንና ዘመን ከዘመን ተሻግሮ፤ ትውልድን በትውልድ አጥፎ 'ዘለዓለማዊ ህልው' ሊያገኝ ቀርቶ - እንደ ጠዋት ጤዛ አረጋገፉ፤ ፋታም አይሰጥ አሚሚቱ። እንዲህ ያሉ - በየዘመኑ የመከኑ ብዕራት፤ በየዘመኑ ነበሩ፤ ዛሬም አሉ፤ ነገም ይኖራሉ። ታዲያ ለመንደርደሪያ፤ የመካነ ብዕራትን ህይወተ ጎዳና፤ ብናነሳሳም ቅሉ፤ የቅኝታችን ሰበቅ ግና - ወዲህ ነው ውሉ።

በኢትዮጵያ የሥነ ፅሁፍ ታሪክ ግዙፍ አሻራ ካኖሩት አንጋፋ ፀሀፍት አንዱ፤ ሣህለ ሥላሴ ብርሃነ ማርያም ይገኛሉ። ሥራዎቻቸው ሕያው ናቸው። ያልመከኑ፤ የማይመክኑ። ደራሲ ናቸው። ተርጓሚ ናቸው። ሀያሲ ናቸው። እንዲህ ይላሉ፤

*በደርግ ዘመነ መንግሥት ኢጋማሽ ላይ አንድ ቀን ዶክተር ፈቃደ አዘዘ (የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መምህር) ስለ እኔ ሕይወት በአጭሩ ለተማሪዎቹ ንግግር እንዳደርግለት ጋበዘኝ። ጥያቄው ሳያስገርመኝ አልቀረም። ስለ እኔ ሕይወት ለማወቅ የሚፈልግ ሰው በእርግጥም አለ ወይ? ስል አሰብኩ።*

አዎ! የሥነ ፅሁፍ ተጠባቢን - ከፍኖተ ሕይወቱ ትሩፋት ለማወቅ፤ ለመማርና ለመጠበብ የምንሻ እንዴት አልነበርን? ነበርን እንጂ! እንዴት አንኖር? አለን እንጂ።

ሣህለ ሥላሴ ብርሃነ ማርያም በዘመነ ደርግ ለቀረበላቸው ጥያቄ ህሊናቸው ተገርሞ፤ ራሳቸውን ቢጠይቁም፤ ይኸው ግጥምጥሞሽ ስላሳደረባቸው ስሜት ሲገልፁ፤ *...ከዚያ በፊት ስለ ሕይወቴ ደፍሬ ለመፃፍ ሃሳብ ኢድሮብኝ ባያውቅም ያን ቀን ግን ሀሳቡ በህሊናዬ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ የተፀነሰ ይመስለኛል፤* ብለዋል በግለ ታሪክ መፅሀፋቸው ቅድመ ትረካ።

እሰየው፤ እንኳንም ተፀነሰ። ፅንሱም ተወልዷልና።

እርግጥ ነው - ሰው ሁሉ በሕይወት ዘመኑ፤ የየራሱ ታሪክ ቢኖረውም ቅሉ - ጣትም ከጣት እንዲልቅ፤ የሰውም ፍኖተ ታሪክ እንዲሁ ነው። ለዚህም ነው፤ እንዲህ ያለው ሰው - በኖረበት ማህበረሰብ፤ በኖረበት ትውልድ ያተመውን ልዩ አሻራ፤ ከተጓዘበት የሕይወት ጎራ - ትውልድ ለማወቅ መጣሩ፤ ለሀገር መዘክር ማኖሩ። ለመሆኑ የሣህለ ሥላሴ ብርሃነ ማርያም ሥነ ፅሁፋዊ በረከቶች ምንድን ናቸው? ይዘረዝሯል እንዲህ፤

በ1956 ዓ/ም የሺንጋ ቃያ (በጉራጊኛ/ በእንግሊዝኛ)፤ 1959 ዓ/ም ወጣት ይፍረደው፤ 1961 ዓ/ም አፈርሳታ (እንግሊዝኛ)፤ 1966 ዓ/ም ዋሪየር ኪንግ (እንግሊዝኛ)፤ 1971 ዓ/ም ፋየርብራንድ (እንግሊዝኛ)፤ 1975 ዓ/ም የሁለት ከተሞች ወግ (ትርጉም)፤ 1976 ዓ/ም ባሻ ቅጣው (ታሪካዊ ልብ ወለድ)፤ 1979 ዓ/ም እምዩ (ትርጉም)፤ 1982 ዓ/ም እምቢ ባዮች (ትርጉም)፤ 1983 ዓ/ም መከረኞች (ትርጉም)፤ 1985 ዓ/ም ዕጣ ፈንታ፤ 1992 ዓ/ም ሹክታ፤ 1995 ዓ/ም ያገር ልጅ...እነህና በዚህ ቅኝት ያልተጠቀሱ፤ የሣህለ ሥላሴ ብርሃነ ማርያም የሥነ ፅሁፍ ትሩፋቶች ናቸው - የኢትዮጵያ ሥነ ፅሁፍ ታሪክ ቅርሶች! እነሆ 'ፍኖተ ሕይወት'፤ የደራሲው ግለ ሕይወት ትርክት - የነህ ሁሉ ጉዞ ውጤት ነው።

*ደራሲው ስለ ፍኖተ ሕይወት ሲገልፁ፤ አብዛኛውን ክፍል የራሴን ትውስታ መሰረት አድርጌ የፃፍኩት ቢሆንም እርግጠኛ ያልሆንኩባቸው ነጥቦች ሲኖሩ ሰዎችን አማክሬአለሁ። የኢትዮጵያንም ሆነ የቤተ ጉራጌን ታሪክ በሚመለከት ግን እዚህ ውስጥ (በመፅሀፉ) የሰፈረው ሁሉ የረጅም ዓመታት ጥናት ውጤት ነው ለማለት እደፍራለሁ።*

*የህይወት ታሪኩን የሚፅፍ ማንኛውም ሰው ሁሌም ፈተና አለበት።...ሁሉንም ዘርዝሮ ማቅረቡ ግን አላስፈላጊ ከመሆኑም በላይ አንባቢን ሊያሰለች ይችላል።...ፍኖተ ሕይወትም በዚሁ መንፈስ የተደረሰ መሆኑን ላረጋግጥ እወዳለሁ፤* ይላሉ ደራሲ ሣህለ ሥላሴ ብርሃነ ማርያም በ2000 ዓ/ም ለንባብ ባበቁት መፅሀፋቸው።

እንግዲህ እኛም ከፍኖተ ሕይወት እየጨለፍን የአንጋፋውን ደራሲ ተርጓሚና ሀያሲ የሕይወት ጉዞ ላልተደረሰ ተደራሲ ለማድረስ እንደሚከተለው ቃኝተናልና ወደዚያው እናምራ።

# ክፍል አንድ

## <u>ከቤተ ጉራጌ እስከ ባህር ማዶ</u>

### <u>1. ውልደትና እድገት</u>

በቤተ ጉራጌ በቸሃ ወረዳ ሲስ ተብሎ በሚጠራው መንደር በ1928 ዓ/ም ከአባታቸው ዳዳ አናንቃ፤ ከእናታቸው ከእመት ኧረሰብ ኬራን ተወለዱ። ልጆች የሞሉበት፤ ቤተ ዘመድ የበዛበት፤ በረከት የወረደበት፤ ፍቅር የሰፈነበት - ነበር የዳዳ አናንቃ ቤተሰብ።

ሣህሌ ስለ አባታቸው በስፋት በፃፉት ፍኖተ ሕይወት ትርከት እንዲህ ይላሉ፤ *መሬቱን ደድቀው፣ እንስቱን ተክለው፣ ቡናውን አብቅለው፣ ጤፉን ስንዴውን ገብሱን በቆሎውን አምርተው፣ ከብቱን በጉን ፍየሉን አርብተው፣ መላውን በላተኛ ሕዝብ በተለይም የከተማውን ነዋሪ ከሚመግቡት የኢትዮጵያ ገበሬዎች አንዱ ናቸው - ወላጅ አባቴ ዳዳ አናንቃ።*

አዎ፤ እውነት ነው። የኢትዮጵያ ገበሬ ያኔም ከዚያም በፊትም መላውን በላተኛ ህዝብ ይመግብ ነበር። ዛሬም በኛ ዘመን መላውን በላተኛ ህዝብ ይመግባል። የእርሱ ህይወት ግን ከዘመን ዘመን እየወረደ ሄዶ እነሆ በእኛ ዘመን ከገባርነት ወደ ዘመናዊ ባርነት አሽቆልቁሏል። ለቻይናው፤ ለህንዱ፤ ለሳውዲው ዲታ ከነመሬቱ ተቸብችቧልና...

ፍኖተ ሕይወት ያወጋን የዚያን ዘመኑ የቸሃው ገበሬ ዳዳ አናንቃ እንደ ድምሩ ገበሬ ግን አልነበሩም። ሀብት አላቸው። ሹመት አላቸው። የተከበሩ ናቸው። እናም እሳቸውን ተገን አድርገውና ተጠግተው የሚኖሩ ሌሎች ገበሬዎችም ነበሩ። እንዲህ ይተርካሉ ልጃቸው፤ *...አባቴ ዳዳ አናንቃ በአኗኗራቸው በጣም ቁጥብ ናቸው። ብር አለኝ፣ ከብት አለኝ፣ መሬት አለኝ፣ ቡናና ባህር ዛፍ አለኝ ስለዚህ ተንደላቅቆ ልኑር የሚሉ ሰው አይደሉም። በዕለት ተዕለት ኑሯቸው በአካባቢያቸው ካለው ገጠሬ በምንም አይለዩም። እሳቸው ከሌሎች የሚለዩት ቁም ነገር በማሰባቸውና በመስራታቸው ብቻ ነበር።*

የሣህሌን የልጅነትና የወጣትነት ዘመነ ታሪክ ስናነብ አባታቸው ዳዳ አናንቃ በሰብዕና ግንባታቸው ዘላቂና ቋሚ መልካም ተፅዕኖ ማድረጋቸውን እንረዳለን። ቀጣዩን ያስተውሏል፤

*አባቴ ዳዳ አናንቃ ከሁለት መቶ ያላነሱ የዳልጋ ከብቶች ነበሯቸው። እኛ ዘንድ የነበሩት ከአስር እስከ አስራ አምስት ይደርሱ ነበር። ከሃምሳ እስከ መቶ የሚሆኑት ደሞ አበሽጌ ከተባለ የሳር አገር ለርቢ ተወስደው እዚያ ይታገዱ ነበር። የተቀሩት (አንድ መቶ ያህል የሚሆኑት) ግን ለድሆች ገበሬዎች ወኪያ ተሰጥተው ነበር። በዚህ ምክንያት ህብረተሰቡ <ዳዳ> የተሰኘውን የከበሬታ (የማዕረግ) ስም ለአባቴ ሰጣቸው።*

*ዳዳ አናንቃ ወኪያ በመስጠት በቸሃ ምድር ብቻ ሳይሆን ከዚያም ውጪ በሰባት ቤት ጉራጌ ከመታወቃቸውም በላይ በየዓመቱ በመስቀል በዓል ሰሞን የእርድ ከብት እንዲሰጧቸው የሚለምኗቸው ዘመድ ወዳጆቻቸው በቁጥር ጥቂት አልነበሩም። የእርድ ከብት ወስደው በዓሉን በደስታ አክብረው በሚገባ ተደራጅተው በመኸር ወራት የከብቶቹን ዋጋ ይመልሱላቸው ነበር።*

*ሥርግ መደገስ ያቃተው ወላጅ፣ ልጅ ሞቶበት መገነዣ ያጣ ድሃ፣ ለመነገድ እጅ ያጠረው ዘመድ አዝማድ ዳዳ አናንቃ ዘንድ መጥቶ ርዳታ ወይም ብድር ይጠይቅ ነበር። እሳቸውም አያሳፍሩትም፣ የተቻላቸውን ሁሉ ያደርጉለታል። በዚህ ሁሉ ምክንያት ዳዳ አናንቃ በህዝብ ዘንድ ተወዳጅ ነበሩ፣* ይላሉ ሣህሌ ልጃቸው ።

<ዳዳ> ህዝባዊ ማዕረግ ወይም ሹመት እንጂ መንግሥታዊ ማዕረግ አይደለም። በቤተ ጉራጌ ህዝባዊ ሹመቶች ወይም ማዕረጎች የተለያዩ መጠሪያዎች ሲኖሯቸው 'ማዕረጋቱ ወይም ሹመቶቹ' ለተባዕት ብቻ ሳይሆን ለእንስትም የሚሰጡ እንደነበሩ ፍኖተ ሕይወት ይተርካል።

በእርግጥም ገበሬው ዳዳ አናንቃ ጥልቅ ሰብዕና ተወዳጅና ተከባሪም ሥነ ምግባር የነበራቸው የቤተ ጉራጌ ማህበረሰብ ኩራት ነበሩ። እንዲህ ያሉ የሀገርና ያካባቢው ህዝብ አድባራት የሆኑ ብዙዎች ነበሩ፣ በየማህበረሰቡ።

ደራሲው ያካፈሉን የዚያን ዘመኑ ታሪክ እኛ የምንገኝበት ትውልድም ሆነ ቀጣዩ ትውልድ 'የጣፋጭ ህልም ዓለም' ታሪክ እንጂ ዕውን ቀደምት ትውልድ ያለፈበት ታሪክ ነው ብሎ ለማመን ይዳዳዋል። አይፈረድበትም። የዛሬው ታሪካችን ከቶም የዚያ ዘመን ተፃራሪ ሆኖ ይገኛልና…

ፍኖተ ሕይወት ዳዳ አናንቃን ሲያስተዋውቀን በእሳቸው ጥላ የቤተ ጉራጌን ታሪክ፣ ባህልና ሥነ ማህበረሰብ ህይወተ ታሪክ ጨምሮ እያንሰላሰለ፣ እያማለለ ይዞን ይገባል - ከቸሃ፣ ከእዣ፣ ከእምድብር…

ለመሆኑ ዳዳ አናንቃ ከቸሃ ባሻገር በሰባት ቤት ጉራጌ ጭምር የታወቁበት <ወኪያ> ምን ማለት ይሆን? እነሆ ፍኖተ ሕይወት እንዲህ ይተርክልናል፣ *…በቤተ ጉራጌ በሰፊው የታወቀ አንድ ባህል አለ። <ወኪያ> ተብሎ ይጠራል። ወኪያ ማለት የከብት አገልግሎት ስጦታ ማለት ነው።* ***በቤተ ጉራጌ የብዙ ከብቶች ጌታ የሆነ ሰው ከብቶቹን በሙሉ ለራሱ አገልግሎት አያውላቸውም።*** *አስር ወይም አስራ አምስት የሚሆኑትን ለራሱ አገልግሎት ያውልና የተቀሩትን ለድሆች ገበሬዎች ያውላቸዋል። ንብረታቸው ሁልጊዜም የሱው ሆነው ይቀጥላሉ። ቢሞቱም ወኪያ ወሳጁ ቆዳውን ገፍፎ ለባለቤቱ የመመለስ ግዴታ አለበት። ተዋልደው ከተራቡ ግን ወኪያ ወሳጁ በውጤታቸው በነፃ ይገለገላል። ወተታቸው፣ ቅቤአቸው፣ አሬራቸው፣ አይባቸው፣ አጓታቸው በሙሉ ለእሱ ጥቅም ይውላሉ። እንዲሁም ከፍተኛ ጥቅም የሚያስገኘው አዛባቸውን ለመሬቱ ማልሚያ ይጠቀምበታል፣ አገር ወለድ ወይም ተፈጥሯዊ ማዳበሪያ ነውና!*

አወይ ባህል! አወይ መተሳሰብ! አወይ መደጋገፍ! አወይ ህዝብ…ይህ ሁሉ ታዲያ በኛ ዘመን የት ገባ? ምን እንክትክት ስብርብር አደረገው? ዛሬ በኛ ዘመን በቤተ ጉራጌ የትኛው አንጡራው ኢትዮጵያዊ ገበሬ ነው ቡና በቅቤ የሚጠጣው? ድፎ እርጎ ሚጥሚጣ ነስነስ አርጎ የሚቆርጠው? ተወዳጁ የእለት ምግቡ አይቤ በጎመን እንደ ዓመት በዓል ምግብ ከናፈቀው ስንት ዘመን ሆነው? የትኛው የቤተ ጉራጌ ገበሬ ነው በዚህ ዘመን መስቀልን ሰንጋ ጥሎ ቅርጫ ገብቶ…ክትፎ በቆጮ የሚንበሸበሸው?…ይህ ሁሉ ድሮ ቀረ። ለምን ቀረ? ማን አስቀረው? ወይስ ለመቅረቱ ማን ምክንያት ሆነ?…የለውጥ፣ የአብዮት ውጤቱ፣ ይህ ከነበረ ግብዓቱ…ምናለ ባይለወጥ በቀረ…በነበረበት በዳከረ…እንደ ኤሌ እያዘገመ በኖረ…

ግና፣ የሆነው ሁሉ ሆኗልና…ፀፀታችንን እንግታና፣ እንመለስ ወደ ፍኖተ ሕይወት። ሳህሌ ካንቆረቆሩት የልጅነት ዘመን ትውስታዎቻቸው መኻል የሚከተለውን ደግሞ ያስተውሏል።

*የአባቴ ጥገኛ /ከሆኑት/ ገበሬዎች ሁሉ ትዝ የሚለኝ ከእኛ መንደር በእግር ግማሽ ሰዓት ያህል ከሚያስኬድ ስፍራ፣ በወንዚር መንደር ይኖር የነበረው አብዬ ንዳ ነው። አባቴ ወኪያ ስለሰጡት በጣም ይወዳቸው ነበር፣ ያከብራቸውም ነበር። በሳምንት ሁለት ወይም ሶስት ቀን ጠዋት ጠዋት እኛ ዘንድ መጥቶ ቡና ይጠጣል፣ ቁርስ ይበላል። ፍፁም ቤተኛ ነው። ከሁሉም ከሁሉም እሱን የማስታውስበት ነገር አለ። በክረምት ወራት እኛ ዘንድ ሲመጣ በሲስና በወንዚር መኻል ባለው ሰፊ የከብት መዋያ ሠረጌ አልፎ አልፎ ከሚታዩት ጉብታዎች እየተሯሯጠ ሄዶ እንጉዳይ ሰብስቦ ያመጣልኝ ነበር። ልጅ ሆኜ ከወተት ቀጥሎ እንደ እንጉዳይ የምወደው ነገር አልነበረም። አብዬ ንዳ ያመጣልኝን እንጉዳይ ምጣድ ላይም ሆነ ፍም ላይ ጠብሼ አነክተው ነበር። አቤት መጣፈጡ! አንዳንድ ጊዜም እናቴ የእንጉዳይ ክትፎ አዘጋጅተው ያቀርቡልኝ ነበር - ይሉናል።*

ሕይወት አንዳንዴም መታደልን ትሻለች። ሣህሌ እድለኛ ናቸው፣ ቢያንስ በልጅነት ህይወታቸው። አብዬ ንዳ ለታዳጊው ሣህሌ ያመጣለት ስለነበረው እንጉዳይ - ቃናውና ጥፍጠቱ፣ ይባስ ብሎ ክትፎነቱ - እንዴት እንደሆን ልንመሰክር የምንችል ስንቶቻችን ነን? ብናውቀው - እንጉዳይን - ጥሩ ነበር።…'እንጉዳዬ ነሽ' እየተባለ ሲዘፈን ሰምተናልና…

ደራሲው በፍኖተ ሕይወት ትርክታቸው ካካፈሉን ሰፊና ተምሳሌያዊ ትውስታዎቻቸው መኻል አንዱ የእናታቸው የእመት ኋሪሰብ ኬራጎ ትውስታቸው ነው። ለአብነት የነቀስነውን እነሆ፤ *...የእዣ ተወላጅ ናቸው፤ የነግየራ ጥብ (ጎሳ)። በዚህም በጣም ይኮሩ ስለነበረ ብዙ ጊዜ የሚያንጎራጉሩት የሰዎቻቸውን ዝና በማንሳት ነበር።*

*<ሹክታ> በተሰኘው መፅሀፌ ውስጥ <ገጣሚነት> በሚል ርዕስ ካቀረብኳቸው ሥነ ቃላዊ ግጥሞች መኻል የእዣ ተወላጅ ስለሆነው 'ላሙ' የተገጠሙት ሁለት ግጥሞችና ስለ አንዛ ኖርያ የተገጠመው ግጥም ከእርሳቸው የሰማኋቸው ነበሩ።*

ሣህሌ ያጫወቱን የእመት ኋሪሰብ ባህሪ በዘመኑ የነበሩ እናቶችን ባህሪ ያስታውሳል። ለተወለዱበት ጎሳ ያላቸው ፍቅርና ክብር መግለጫው እንዴት እንደነበር ሣህሌ ሲያወጉን በተመሳሳይ የህይወት ጅረት ያለፉ ሁሉ በየራሳቸው ቤተሰብ ውስጥ የነበረውን ህይወት ማሰላሰል ግድ ይላቸዋልና። እርግጥ ነው በየብሄረሰቡ መክነው የቀሩ ወይም ለተከታዩ ትውልድ ያልተላለፉ የሥነ ቃል ግጥሞች፣ ተረቶች፣ አባባሎች...በርካቶች ናቸው። በዚህ ረገድ ሣህሌ ቢያንስ በብሄረሰቡ ውስጥ ይዜሙ ወይም ይነገሩ ከነበሩት የጥንት ዘመን የሥነ ቃል አካል ግጥሞች መኻል በእናታቸው አማካይነት የሰሙትን በቅርስነት በሰነድ ማኖር መቻላቸው ያስመሰግናቸዋል።

እመት ኋሪሰብ ትዳር ስለያዙበት ሁኔታም ለልጃቸው ሲያጫውቱ እንዲህ ብለዋል፤ *ልጅ ነበርኩ ስዳር፣ የአስራ ስድስት ዓመት ወጣት። አባትህን አላውቀውም፣ በዚያን ጊዜ። አባቴም በጣም ይወደኝ ነበር። የሠርጉ ዕለት ሲቃረብ 'በምትዳሪበት ቀን እንዳታለቅሺ ልጄ፣ አንቺ ካለቀስሽ እኔም ሆድ ብሶኝ ማልቀሴ አይቀርም። ስለዚህ እኔን አስለቅሰሽ እንዳታዋርጂኝ የሰው መሳቂያ እንዳታደርጊኝ' አለኝ።...መቼም ስትዳር የማታለቅስ ልጅ በአገር ምድሩም የለም፣ በዚያን ጊዜ። እኔ ግን አባቴ አስጠንቅቆኝ ስለነበረ እሱን እንዳላስለቅስ ፈርቼ ሳላለቅስ ቀረሁ።*

*እዚህ ይዘውኝ ከመጡ በሁዋላ አባትህን ባየው ጠና ያለ ሰው ነው። የግንባሩ ፀጉር ግራና ቀኝ ገባ ገባ ብሏል። ጥዬው ለመኮብለል ቃጣኝ። እብድ ነበርኩ፣ በዚያን ጊዜ። ግን ኮብልዬ የት ልገባ? አባቴ እንደሆነ አንዴ ለሰው ሰጥቶኛልና አያስገባኝም። ስለዚህ ሃሳቤን ቀይሬ እዚሁ ቀረሁ። አሁን ሳስበው ግን አይቆጨኝም። አንተን፣ እህቶችህንና ወንድሞችህን ስለወለድሁ።*

ይህ የእመት ኋሪሰብ ኬራጎ ታሪክ የብዙዎቻችንን ቤት ያንካኳል። እንደ እውነቱ ከሆነ በዚህ ዘመን በሰነበተ የእድሜ ክልል ላይ ከምንገኝ ትውልዶች እንዲህ ያለ ወይም ተመሳሳይ ታሪክ ያወጉልን እናቶቻችን ስንቶች ናቸው? ምናልባት ሁሉም!

አዎ፤ የዚያን ዘመን እናቶች ጋብቻቸው ይመሰረት ወይም ይፈፀም የነበረው እንዲህ ነበር። ሳይተዋወቁ ይፈጣጠማሉ። ሳይተያዩ ይነፋፈቃሉ። ሳይቀራረቡ ይጋባሉ። ተጋብተው ይተዋወቃሉ። ተላምደው ይፈቃቀራሉ። ጎጇቸውን አሙቀው ወልደው ይከብዳሉ። በፍቺ ወረርሽኝ ያልተለከፉ፤ በመቻቻልና ይቅር ባይነት ልቦናቸውን ያሰፉ...በኑሮ ጀልባ እየቀዘፉ፤ በእድሜ ጅረት እየሰፈፉ፤ እኛን ተከተው ያለፉ...የአብናቶቻችን ትዳር፤ እንዲህ ነበር - በጉራጌው፤ በኦሮሞው፤ በአማራው በትግራዩ፤ በደቡቡ፤ በምዕራቡ፤ በምሥራቁ...

## 2. ሀ - ሁ፤ በሰንበሌጥ

ደራሲ፤ ተርጓሚና ሃያሲ ሣህለ ሥላሴ ብርሃነ ማርያም - እኒህን ሁሉ ከመሆናቸው አስቀድሞ የፊደል ዘር የዘሩባቸው፤ የዕውቀት ማረሻ እርፍ ያስጨበጧቸው - አባታቸው ዳዳ አናንቃ ነበሩ። ሣህሌ እንዲህ ይላሉ፤*...ስለ ዳዳ አናንቃ ብዙ የሚያስገርሙኝ ነገሮች አሉ። ከእነዚህ አንዱ በዚያ እልም ባለው ገጠር ውስጥ እየኖሩ አማርኛ ማንበብና መፃፍ መቻላቸው ነበር። አማርኛ ቋንቋ ይሰማሉ፤ መናገር ግን እጅግም አይሆንላቸውም። የማንበብና የመፃፍ ችሎታ ግን ነበራቸው። ሲያነቡ እጅግ ቀሰስተኛ ነበሩ።...*

*አንድ ቀን ጠዋት በአንደኛው መፅሀፋቸው ውስጥ የነበረውን ፊደል ገልጠው 'ሰንደዶ ቢጤ ይዘህ ና' አሉኝ። በከብቶቻችን ፊት ከተከመረው ሳር ሰንደዶ ቢጤ የሳር ዘለላ አነሳሁና ለአባቴ ወስጄ ሰጠኋቸው። 'ቁጭ በል' አሉኝና በሰንደዶ ቢጤው የመጀመሪያውን ፊደል ጠቁመው <ሀ> አሉ።*

*እኔም ድማፃቸውን ተከትዬ <ሀ> አልኩ። <ሁ> ሲሉ <ሁ> እያልኩ እስከ <ሆ> ደረስን።...እንደ በቀቀን ያሰሙኝን ፊደል ድምፅ እየደገምኩላቸው እስከ <ፐ> እና <ፖ> ደረስን።*

እነሆ ገበሬው ዳዳ አናንቃ ልጃቸውን <ሀ> በል አሉት - የፊደል ዘር፤ የቋንቋ ልሳን ሊያናግሩት፤ ሊያሳውቁት። ተማር አሉት የፊደል ዘር እወቅ። እንጂ ቋንቋ ጨቋኝ ነው፤ ቋንቋ ነፍጠኛ ነው አልወጣቸውም፤ የፊደል ዘር ሲዘሩ፤ <ሀ> እና <ፐ>ን ሲያስቆጥሩ። ፍኖተ ሕይወት እንዲህ ይላል፤

*ከዚያን ቀን ጀምሮ በየቀኑ ፊደሉን ያስጠኑኝ ገቡ፤ የመጀመሪያው መምህሪ ዳዳ አናንቃ። ከሶስት ወይም ከአራት ወራት በሁዋላ መላውን ፊደል በቃሌ ያዝኩት። ጉዴ የፈላው አቡጊዳ መማር ስጀምር ሆነ። ለካስ ፊደሉን በቃል ያዝኩት እንጂ በመደዳ ሳይሆን አመሰቃቅለው 'ይህ ምንድን ነው?' ሲሉኝ ትክክለኛውን መልስ መስጠት አልችል ኖሯል! ጆሮዬን ቁንጥጥ እያደረጉ 'እያንዳንዱን መለየት አለብህ፤ ዝም ብለህ በቃል መድገሙ ዋጋ የለውም' አሉኝ - ይሉናል የአናንቃ ተማሪ።*

ብዙዎቻችን 'ፊደል ሠራዊትን' በጅምላ ተሰብስበን ያነበነብነው - የዬኔታን አለንጋ በአንድ አይናችን እየጠበቅን እንደነበር ትዝ ሲለን፤ ሣህሌ ግን በአባታዊ ቁንጥጫና ምክር ታጅቦ <ሀ> ብሎ <ፐ>ን ዘለቆ <አቡጊዳ>ን ማስጎብደዱ - ዳዳ አናንቃን በመታደሉ።

እውነት ብለዋል፤ ዳዳ። እንደ በቀቀን የተማሩትን ማነብነብ ሳይሆን - እውቀት ማለት፤ ማስተዋልና መለየት ማለት መሆኑን ገና ከጠዋቱ ከትውልድ መንደሩ ከሲስ ሳይወጣ፤ እዛው ቤቱ ነበር በቁንጢጥ ጭምር የሣህሌን መሰረት የገነቡት አባቱ ዳዳ አናንቃ። የፊደል ዘር የዘረዘረው ሣህለ ሥላሴ መፃፍም የተማረው በአናንቃ አዝማችነት ሲሆን ፍኖተ ሕይወት በትውስታ ሲያወሳ፤ *...ፊደሎቹን መለየት ስጀምር ከአመልካች ጣት የማይበልጥ ቁራጭ እርሳስ ሰጡኝና ኢያያዙንና አፃፃፉን አስተማሩኝ። ከዚያ ወዲያማ በምኑም በምናምኑም ላይ እፅፍ ጀመር። ጭኔ ላይ በጥፍሬ እሞነጫጭራለሁ። የኮባ ቅጠል፤ ፀሀይ የማያየው ወገኑ ዱቄት የመሰለ ነጭ ነገር ስላለው በስንጥር ሲነኩት ምልክት ይተዋል። ጊደሮቻችንን ውሃ ለማጠጣት ወደ መጊየቻ ወንዝ በምንወርድበት ጊዜ በወንዙ ደለል ላይ በዘንጌ እፅፋለሁ። እንዲሁም ከምጣድ ቂጥ ጥላሸቱን ፈቅፍቄ አውርጄ በውሃ በጥብጬ ጥቁር ቀለም እሰራና እኔው ከመቃ በቀረፅኩት ብእር አጥቅሼ ብጣሽ ወረቀት ላይ እፅፍ ነበር፤ ይለናል።*

ወይ ጊዜ! ለሁሉም ጊዜ አለው፤ አይደል መፅሀፉስ ያለው? ኮባም ጊዜ ነበረው። ጥላሸትም ጊዜ ነበረው። ደለልም ጊዜ ነበረው። እነሆ ደግሞ ጊዜው የኮምፒዩተር ሆኗል...በኮባና በጥላሸት የፃፈው ታዳጊው ሣህለ ሥላሴም አድጎ እነሆ ወረቀት አይበቃው ደራሲ ሆኖት አረፈው። ለሁሉም ጊዜ አለው፤ ማለት ይኸው አይደል?

## 3 እምድብርና አባባ ባሪቅየ

ደራሲ ሣህለ ሥላሴ ብርሃነ ማርያም ተወልደው ካደጉበትና የፊደል ዘር ከለዩበት ሲስ መንደራቸው ወደ እምድብር ከተማ ለትምህርት እንደተላኩ ባወጉበት ትርክታቸው አስደማሚና መሳጭ ገጠመኞቻቸውን በስፋት አውርደዋል። እነሆ አብነት፤

*የዚያን ጊዜው እምድብር (በ1937 ዓ/ም) ሁለት መልክ ነበረው፤ ከተማና ገጠር። የከተማው ነዋሪዎች ግማሾቹ አማርኛ ተናጋሪዎች (በአፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት የመጡ ነፍጠኞች ተወላጆች) እና ግማሾቹ ጉራጊኛ ተናጋሪዎች ነበሩ። የነፍጠኞቹ ተወላጆች የሚናገሩት አማርኛ በጣም አስቂኝ አይነት ነበር። የጠራ አማርኛ ነው እንዳይባል የጉራጊኛ ድምፀት የተቀላቀለበት ነበር። የጠራ ጉራጊኛ ነው እንዳይባልም የአማርኛ ድምፀት የተቀላቀለበት ነበር። ለምሳሌ <ቄንሳ> ብለው የሚጠሩት ቃል ነበራቸው። ትርጉሙ በትክክለኛው አማርኛ <ኣይብ> ማለት ሲሆን በትክክለኛው ጉራጊኛ ግን <ቂየሳ> ነው። እነሱ ግን <ቄንሳ> ብለው ይጠሩታል። እንዲሁም ብዙ አዳዲስ ቃላት ፈጥረው ይጠቀሙ ነበር። አሁን አሁን ሳስበው አዳዲስ ቀበልኛዎች የሚፈጠሩት ምናልባት በዚህ አይነት ነው ወይ ያሰኘኛል። በቤተ ጉራጌ ደግሞ በጣም በርካታ ቀበልኛዎች እንዳሉ ይታወቃል፤* ይላል ፍኖተ ሕይወት።

ይህ በእምድብር አልፎም በመላው ቤተ ጉራጌ የሚገኘው የነባሩና የመጤው ማህበረሰብ/ብሄረሰብ ስብጥርና አኗኗር፤ ቋንቋ ባህል ወግና የሥነ ልቡና አደረጃጀት በድፍን ሸዋ በአርሲ በወለጋ በሲዳማ በከፋ በኢሊባቡር በሐረርጌ...ሁሉ ውስጥ የኖረና ያለ የኢትዮጵያ ሥነ ማህበረሰብ ህይወት ነባራዊ እውነታ ነው። በምኒልክ ሠራዊት (በዘመኑ አጠራር ነፍጠኛ) እና ሠራዊቱ በሰፈረባቸው በነባሩ ማህበረሰብ መካከል በትውልድ ሂደት የመዋዋጥና የመበዋወዝ ተፈጥሯዊ ክስተት ተከናውኗል። ይህ የሥነ ማህበረሰብ ታሪክ ሳይንሳዊ ሂደት ህግ ነው። ይህንን የሂደት ህግ አንድ መንግሥት ወይም ብሄረሰብ በቀመረው ወይም በሚቀምረው ፎርሙላ ማጥፋትም ሆነ ወይም ለዘለቄታው ገድቦ በፈለጉት ቦይ እንዲፈስ ማድረግ ከቶም አይቻልም። በሰው ልጆች የእስካሁኑ ታሪክ ይህ ሆኖ አልታየምና።

እነሆም በእምድብር አማርኛ የሚናገሩ ጉራጌዎች ወይም ጉራጊኛ የሚናገሩ አማራዎች መኖራቸው አስገራሚ ሊሆን የማይችለውም ለዚህ ነው። በኢትዮጵያ ብሄረሰቦች መካከል የክልል አጥር አቁሞ አንዱን የብሄረሰብ ክፍል ከሌላኛው ማውጣት አይቻልም። ያኛው ብሄረሰብ በዚህኛው ይህኛውም ብሄረሰብ በዛኛው ውስጥ ተቆላልፈው ኖረዋልና። ለዚህም ነው የማታ ማታ የህወሃት/ኢህአዴግ የዘር ፖለቲካ በህዝብ አንድነት የሚፈታው...የሚመታው! እነሆ ደግሞ ቀጣዩን ታሪክ ልብ ይሏል፤ ከፍኖተ ሕይወት።

*...ሩቅ ሳንሄድ በዳግማዊ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት እንኳ በርከት ያሉ ነፍጠኞች ወደ ጉራጌ አገር መጥተው በእምድብር፤ በየዠንቦራ፤ በዶረገብያ፤ በአዳራሼ፤ በባሩድ ቤት (እነሞር) ሰፍረዋል።* ***እነዚህ ሁሉ በህዝቡ ባህል ተውጠው ቀርተዋል፤ ወይም ጉራጌ ሆነዋል። እንዲሁም የሐረርጌ ጎሳዎች በተለይም በግራኝ አህመድ በአስራ ስድስተኛው መቶ ዘመን ወደ ምሥራቅ ጉራጌ መጥተው ሰፍረዋል። እነዚህም በህዝቡ ባህል ተውጠው ቀርተዋል።***

***መጦቹ በህዝቡ ባህል ተውጠው ቢቀሩም በየበኩላቸው የሰጡት ነገር አለ። የሰሜን ሀበሾች ሴማዊ ቋንቋን ይዘው ከመምጣታቸውም በላይ ክርስትናን ይዘው መጥተዋል። የሐረርጌ ጎሳዎች እስልምናን ይዘው መጥተዋል...***

ከዚህ በላይ የነቀስነው የታሪክ እውነታ ሰበዝ በራሱ ብቻ ብዙ የሚናገርና የሚያሳይ ነው። በተለይም በዚህ ዘመንና ትውልድ ቋንቋን እንደ ጭቆና መሳሪያ አድርጎ ከበሮ በመደለቅ፤ የኢትዮጵያውያንን ህብረ ማህበረሰብ የአብሮነት ህይወት ድርና ማግ ለመበታተን ህወሃት/ኢህአዴግ የሚያራምደውና የሚያራግበው የጎሳ ፖለቲካ ሳጥናኤላዊ ተልእኮና ግብ ከነሙሉ ጥፋቱና ጥላሸቱ ከመቼውም ዘመን በላይ እርቃኑን ቆሞ ይታያል። የህወሃት/ኢህአዴግም ሆነ ወይም አምሳያ አጀንዳንና የጎጥ ፖለቲካን መለያቸው ያደረጉ ሌሎች ጎጠኛ ድርጅቶች የኢትዮጵያን ህዝብ የሚያለሙና የሚያበለፅጉ፤ አብሮነቱን የሚያጠናክሩ፤ ዜግነቱንና ሉዐላዊነቱን የሚያስከብሩ ላለመሆናቸው ከ1983 ዓ/ም ጀምሮ ያለው የኢትዮጵያ ታሪክ ቋሚ ምስክር ሆኗል።

ታሪክን ታሪክ ያነሳል ሆነብንና ፍኖተ ሕይወትን አስታከን ያነሳሳነውን የታሪክ ነቁጥ በዚሁ እንግታና እንመለስ ወደ ቅንታችን። ለመሆኑ እምድብር የወጣው ታዳጊው ሣህለ ሥላሴ ትምህርቱ ከምን ደረሰ? ብለን እንጠይቅ። *...እምድብር እንደወጣሁ ፊደል አስተማሪ የነበሩት 'አባባ ባሪቅየ' (አባባ ሽሜ) ብለን እንጠራቸው የነበሩ መምህር ወልደሩፋኤል ፈተና ሰጡኝ። ንባቡን አንበለበልኩላቸው። በጣም ተደስተው 'አንተ ፊደል ቤት ሳይሆን ሶስተኛ ክፍል ነው መግባት ያለብህ' አሉኝ። አማርኛ ትንሽ ትንሽ እሰማለሁ እንጂ በቅጡ አልናገርም። ማንበብ እችላለሁ እንጂ ያነበብኩት ምንባብ ፍቺው ምን እንደሆነ አይገባኝም። በዚህ ላይ ሂሳብ የሚባል ነገር ፈፅሞ አልጀመርኩም። ሶስተኛ ክፍል የነበሩት ተማሪዎች ግን አራት መደብ ሂሳብ የሚማሩ ነበሩ...ሲል ያወጋናል ፍኖተ ሕይወት።*

እንግዲህ አባባ ባሪቅየ ማለት እኛ በከተማው ለምሳሌ በአዲስ አበባ 'የኔታ' እምንላቸው ፊደል አስተማሪ አይነት መሆናቸው ነው። ታዲያ ዳዳ አናንቃ እየመከሩና ጆሮውንም እየቆነጠጡ የፊደል ዘር የዘሩበት ሣህሌ እምድብር ወጥቶ አባባ ሽሜ ፊት ንባቡን እንደ መትረየስ ቢያንጣጣባቸው - ሁለት ክፍል 'አንከረባብተው' ሶስተኛ ክፍል ዶሉት - እምድብር ቀዳማዊ ሃይለ ሥላሴ አንደኛ ት/ቤት። አማርኛ ቋንቋ በቅጡ መስማትም ሆነ መናገር ወይም ያነበበውን መረዳት የማይችለው ሣህሌ ጉድ ፈላበት ይሆን? ፍኖተ ሕይወትን እናቀርባለን፤

*...አባባ ባሪቅየን ምን ጊዜም አልረሳቸውም። እኚህ አስተማሪያችን በእድሜ በጣም የገፉ፤ ፀጉር የሚባል ነገር የሌላቸው፤ በዚህም ምክንያት ራሳቸው ላይ ሁል ጊዜ ሻሽ የሚጠመጥሙ፤ ጥርሶቻቸው የረገፉና ምራቃቸው ሰው ላይ እንዳይበተን ሲናገሩ አፋቸውን በመዳፋቸው ሸፈን የሚያደርጉ፤ በጣም ደግ ሰው ነበሩ። አማርኛዬን እንዳሻሽል አስበው ለአንድ ሳምንት ያህል እሳቸው ዘንድ እንድቀመጥ አደረጉ።...ስሜ የሚባል /አብሯቸው የሚኖር/ ረዳት ነበራቸው። ሁለቱም / አባባ ባሪቅየና ስሜ/ የጉራጊኛ ቋንቋ አያውቁም...*

*/የመጀመሪያው/ ቀን ሌሊት ጉዴ የፈላው ራታችንን በልተን ከጨረስን በሁዋላ ነበር። አባባ ባሪቅየ ወደ አልጋቸው ሄደው ጋደም ብለዋል። ስሜ ለእሱና ለኔ ኬሻ አንጥፏል። አባባ ሽሜ ከአሉበት አልጋ ላይ ሆነው <ተኛ> አሉኝ። ከዚያን ቀን በፊት ይህን ቃል ሰምቼው አላውቅም። ምን ማለታቸው እንደሆን ግራ ገባኝ። <ተኛ> አሉኝ መልሰው። <ና ወዲህ> ያሉኝ መስሎኝ እሳቸው ዘንድ ብሄድ በድዳቸው ሳቁና <ሂድና ወዲያ ተኛ> አሉኝ። ስሜ ጋ ሁጄ አይኖቼን አቁለጨልጭ ገባሁ። አሁንም ምን እንዳደርግ እንደተፈለገ አልገባህ አለኝ። አባባ ሽሜ አሁንም በድዳቸው እየሳቁ አንዱን ጉንጫቸውን በመዳፋቸው ይዘው የመተኛት ምልክት እያሳዩ <ተኛ> አሉኝ። ግራ መጋባቴን የተረዳልኝ ስሜ በመጨረሻ እጄን ስቦ ኬሻው ላይ አመለከተኝና <ተኛ> አለኝ። ሁለቱም ምን ማለታቸው እንደሆን በዚህ ጊዜ ገብቶኝ ኬሻው ላይ ጋደም አልኩ...ይሉናል ደራሲው።*

ይህ የደራሲ ሣህለ ሥላሴ ትውስታ በብዙ ፈርጅ የኢትዮጵያን ማህበረሰብ ህይወት በተለይም የአማርኛ ቋንቋን አበታተን ወይም ስርጭት ሂደትና እድገት በታሪካዊ ክስተቱ ባልወየበና ባልደበዘዘ መስተዋት እንድንመለከት ይጋብዘናል፤ ይገፋፋናልም። በዚህ ዘመን አመጣሽ በሆነው የህወሃት/ኢህአዴግ ፖለቲካ ቫይረስ የተለከፉና አተያያቸውና አፈራረጃቸው ሁሉ እንደጋሪ ፈረስ እይታ የተገደበባቸው ወገኖቻችን በእንደምን ያለ ከዘመንና ከትውልድ ጋር በማይጎዳኝ የጥፋት ኩሬ ውስጥ እንደሚገኙም ልብ ለሚያደርግ ልቦና ፍኖተ ሕይወት ይናገራል።

የቤተ ጉራጌ ተወላጁ ዳዳ አናንቃ አማርኛ በማወቃቸው፤ በማንበብ በመፃፋቸው (በተገደበ ደረጃም ቢሆን) ቋንቋው ጨቋኝና የጭቆና መሳሪያ ነው ብለው አያምኑም ነበርና ልጃቸውን አማርኛ አስተማሩት፤ የፊደልን ዘር። አባባ ባሪቅየ ሣህሌን ከዳዳ አናንቃ ተቀብለው - በድዳቸው እየሳቁበት - <ተኛ>ን አስተማሩት። አባባ ሽሜና ስሜ እየተቀባበሉ፤ ሣህሌን ያለመታከት አማርኛ ሲያስጠኑ...<ተኛ፤ ተነስ፤ ተራመድ> እያሉ፤ እነሆ ያ ሁሉ አለፈና - የቸሃው ቡቃያ፤ ከሥነ ፅሁፍ አድባራት የኢትዮጵያ፤ አንዱ ሆነልና። ደራሲ ሣህሌ እንዲህ ይላሉ፤

*አማርኛዬን ለማሻሻል ከሁሉም በላይ የጠቀመኝ ግን በ1962 ዓ/ም የታተመው የደስታ ተክለወልድ 'ዐዲስ የአማርኛ መዝገበ ቃላት' ነው። ይህንን መዝገበ ቃላት አስቸጋሪ ፅንሰ ሀሳቦች ሲያጋጥሙኝ በማጣቀሻነት ከመገልገልም በላይ እንደ ልብ ወለድ መፅሀፍ ከአጎበር እስከ አጎበር ከአንድም ሁለቴ ወጥቼዋለሁ።...ከዚህ መዝገበ ቃላት ያገኘሁት ዕውቀት ከ - እስከ ነው ብሎ ለመግለፅ ይቸግረኛል። የቃላቱን ልዩ ልዩ ፍቺ ከመስጠቱም በላይ ምንጩንም ጭምር ይገልፃል። ከኦሮምኛ ከትግርኛ ከግዕዝ ከጉራጊኛ ወይም ከሌላ ቋንቋ የመጣ እያለ...* በማለት ስለ አማርኛ ቋንቋ እውቀታቸው አንጥበዋል።

## 4 አዲስ አበባ

በቸሃ በሲስ መንደር በሰንበሌጥ ጥቆማ የተጀመረው የዕውቀት ጠብታ በእምድብር ቀዳማዊ ሃይለ ሥላሴ አንደኛ ት/ቤት ቀጥሎ በአዲስ አበባ ላዛሪስት ሚሲዮን፤ በተፈሪ መኮንን ት/ቤት እና በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ (ቀዳማዊ ሃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ) ጠብታው ተጠራቅሞ መዝነም ጀመረ። ሣህለ ሥላሴም እነሆ በዕውቀት ራሰ፤ ረሰረሰ። ፍኖተ ሕይወት የዚህን ዘመን ትውስታ በስፋት ያወጋል። ለቅኝታችን መቅዘፊያ ይሆነን ዘንዳ ጥቂት ብንጨልፍስ?

*...የዘመኑ የአዲስ አበባ ከተማ ዋናው የህዝብ ማመላለሻ ጋሪ ነበር። እነ ኩርኩር (ባለ ሶስት ጎማው መጓጓዣ)፤ እነ አውቶቡስ፤ እነ ሚኒ ባስና ውይይት ገና አልገቡም። ፈረንጆችና ጥቂት ዘበናይ ኢትዮጵያውያን ሹማምንት በታክሲ ይጓዙ እንደሁ እንጂ ሌላው የከተማው ነዋሪ በሙሉ፤ ከእግረኛው በስተቀር፤ በጋሪ ነበር የሚጓጓዘው። ከፒያሳ መርካቶ፤ ከለገሃር ጉለሌ፤ ከአራት ኪሎ ቀበና፤ ከመርካቶ ኮልፌ፤ ወዘተርፈ። ፈረሶቹ አስፋልቱን መንገድ ከኮቴያቸው ስር በተገጠመላቸው የብረት መጫሚያ እያንቋቁ ቂብ ቂብ...ቂብ ቂብ የሚል ድምፅ እያሰሙ ሲያልፉ እስከ ዛሬ ድረስ በውስጥ ጆሮዬ ሲያስተጋባ ይሰማኛል። ስንቱን ጀግና ከጦር ሜዳ እንዳላደረሱ ሁሉ የስንቱን ንጉሥ ስም አባ ዳኘው፤ አባ ዲና፤ አባ ታጠቅ፤ አባ ጠቅል እያሰኙ እንዳላስጠሩ ሁሉ እነ ዳማ፤ እነ ጉራች፤ እነ ቦራ፤ እነ ሻንቆ ጣሊያን ባመጣው ሥልጣኔ ተዋርደው የጋሪ ጎታች ሆነው ቀሩ...*ይላል ፍኖተ ሕይወት ስለዛን ዘመኑ ትውስታውን ሲያወሳ።

አዎ፤ ሀቅ ነው። እነ ዳማ እነ ጉራች እነ ቦራ እነ ሻንቆ...እየሰገሩ፤ እያስፈከሩ፤ እያስጣሉ...ወድቀዋል። ሀገር አስጠብቀዋል። ዳር ድንበር አካልለዋል። አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ባንዲራ ይዘው ተምመዋል...

እውነት ነው፡ እነ ታጠቅ እነ በዝብዝ እነ ዳኘው እነ ጠቅል ወራሪን ገጥመዋል። ከእንግሊዝ፤ ከደርቡሽ፤ ከግብፅ፤ ከጣሊያን።

እውነት ነው፤ እንቢ ለነፃነት፤ እንቢ ለሉዐላዊነት፤ እንቢ ለባንዲራ ብለው በወደቁት አርበኞች ቤዛ ታሪክ ተሰርቷል። ሀገር ቆሟል። ዜግነት ተጠብቋል። ጣሊያን ተደቁሷል።

እርግጥ ነው፤ ተፈጥሮ ያደላቸው፤ ዘርፈ ብዙ ግልጋሎታቸው የእነ ጉራች የእነ ዳማ የእነ ሻንቆ...የትለሌ ነውና፤ እንደ ዘመኑ እንዳኗኗሩ...ወራሪው ጣሊያን ባመጣው ሥልጣኔ ጋሪ ጎታች ስለሆኑ...'እንዴት ተደርጎ!" ብለን - አካኪ ዘራፍ፤ ቡራ ከረዩ፤ ያዙን ልቀቁን ያኔም አላልንም፤ ዛሬም አንልም። ነገር ግን ያኔም ሆነ ዛሬ የምንለው - እነ ዳማ፤ እነ ጉራች፤ እነ ቦራ፤ እነ ሻንቆ፤ እነ ታጠቅ፤ እነ በዝብዝ፤ እነ ዳኘው፤ እነ ጠቅል...ውለታቸው አይረሳ፤ ታሪካቸው አይንኳሰስ አይበወዝ አይከለስ፤ ገድለቸው በአግባቡ ይዘከር ይከበር...እንጂ!

ደራሲ ሣህለ ሥላሴ ብርሃነ ማርያም ካወጉን በአዲስ አበባ የላዛሪስት ሚሲዮን ኑሮ ህይወት ሰፊ ትውስታቸው መካከል የሚከተለውን በጥሞና ያነቧል፤ *...ለአምስት ዓመታት ያህል አብረን መኖር የጀመርነው ወጣቶች ከተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍሎች የመጣን ነበርን። ከቤተ ጉራጌ፤ ከከምባታ፤ ከወላይታ፤ ከአርሲ፤ ከኤርትራ፤ ከትግራይ እና ከአዲስ አበባ ጭምር የተሰባሰብን ነበርን።* ***በመኻላችን የወንድማማችነት ስሜት እንጂ አንድም ቀን የልዩነት ስሜት አድሮብን አያውቅም።*** *የአዲስ አበባዎቹ ግን አማርኛ ስንናገር የቃላት አጠራራችን ወደ እየአፍ መፍቻ ቋንቋችን ስለሚስበን ይስቁብን ነበር። ይህ ግን* ***ለክፋት ሳይሆን መኮለታተፉችን እንደ አስቂኝ ነገር ስለሚቆትሩት ነበር።*** *እና ሁላችንም አብረን ውለን አብረን እናድራለን። እሁድ፤ እሁድ ወደ እንጦጦ እየወጣን ወይም ሸጎሌ ወደተባለው ሜዳ እየሄድን የእግር ኳስ እንጫወታለን...ሲሉ ያወጉናል ሣህሌ።*

በዚህ የፍኖተ ሕይወት ትረካ ውስጥ አሻግረን የምንመለከተው የኢትዮጵያን ማህበረሰብ የህብረ ብሄር ስብጥርን፤ አብሮነትንና አንድነትን ነው። ከሁሉም በላይ ይህ ታሪክ (በዘር ቫይረስ ተመርዘው እንደሚገኙት የቋንቋ ጎጠኞች ሳይሆን) በዘመኑ በከተማው ሁለገብ ቋንቋ አማርኛ ተናጋሪዎችና ከሌሎች ብሄረሰቦች በመጡ ሌላ ቋንቋ አፍ መፍቻቸው በነበሩ ተማሪዎች መካከል የነበረውን ጤናማ የወንድማማችነት መንፈስን አንጥሮ ያሳያል።

ይሁን እንጂ በኢትዮጵያ በአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪዎችና በሌሎች ቋንቋ ተናጋሪዎች መካከል - ቋንቋን አስመልክቶ - የነበረው **የባህል ግጭት** በዘመኑ ከኖረው ሥርዐተ ማህበር ሥነ መንግሥታዊ አደረጃጀትና አመራር ጋር የተጎዳኘ ሆኖ ይገኛል።

በሀገር ግንባታ ሂደት በቀደምት ትውልድ  የተሰሩ ስህተቶችን ሀገር ተረካቢ ተከታታይ ትውልዶች አዎንታዊውን የታሪክ አካል እየተንከባከቡ አሉታዊውን ደግሞ ሀገርና ትውልድን በማያናውፅ፤ በማያናጋ መንገድ እያስተካከሉና እየቀየሩ ትውልዳዊ የዜግነት ሃላፊነታቸውን ሊወጡ ነው የሚገባው። በኢትዮጵያ የብሄረሰብ ቋንቋዎችን እድገት፤ የተናጋሪዎቹንም ሥነ ልቡናና ክብር ከመጠበቅ አኳያ በቀደምት ሥርዐት ግዙፍ ስህተት ተሰርቷል። ያንን ስህተት እያራገቡ መፍትሄው ዛሬ ህወሃት/ኢህአዴግ የቀየሰው ጎዳና ነው የሚሉ ሁሉ ግን በተቆፈረው የጥፋት አዘቅት ገብተው መውጫ ከማጣት በቀር የሚያለሙት አንዳችም ቁብ የለም። ይህም ሀቅ ለመሆኑ ከሁለት አስርታት በላይ በዘለቀው የህወሃት/ኢህአዴግ ፖሊሲ ፍንትው ብሎ ታይቷልና...

ወደ መነሻ ነቁጣችን ስናቀና፤ በባህል ግጭት በአማርኛ ቋንቋ ምክንያት በኢትዮጵያ ተከስቶ ከነበረው ዕውነታ አንፃር ደራሲ ሣህለ ሥላሴ እንዲህ ያጫውቱናል፤ *...አማርኛ ከማይነገርበት ገጠር አካባቢ ወደ አዲስ አበባ የሚመጣ ኢትዮጵያዊ* ***የባህል ግጭት*** *እንደሚደርስበት የችግሩ ሰለባ የሆኑት ሁሉ ያውቁታል።...ይህ ችግር ከቤተ ጉራጌ የመጣነውን ብቻ ሳይሆን እንዲያውም ምናልባት በከፋ መልኩ አማርኛ ተናጋሪ ካልሆኑ ሌሎች የኢትዮጵያ ክፍሎች የሚመጡትን ሁሉ ይመለከት ነበር። ለምሳሌ የእኔ የልጅነት መጠሪያ ስሜ 'ሣህሌ አናንቃ' ሆኖ ሳለ ይህንን* ***የሀገር ቤት ስሜን እንድለውጥ ያደገረኝ የባህል ጫና አጋጥሞኛል።***

***ችግሩ ያለው <አናንቃ> ከተባለው የአባቴ ስም ነበር። የትምህርት ቤት ጓደኞቼም ሆኑ አስተማሪዎቼ ይህንን ቃል በትክክል አይጠሩትም።*** *ድምፁ...በአፍንጫ የሚነገር ነው። አስተማሪዎቼና የት/ቤት ጓደኞቼ (ከቤተ ጉራጌ ከመጡት በስተቀር) ቃሉን <አና-ንቃ> ወይም <አናቃ> ብለው ነው የሚጠሩት። ይህ ደግሞ በሁለቱም መልኩ ትክክል አይደለም።  ስሰማው ለጆሮዬ በጣም ስለሚከብደው ለዚህ ችግር መፍትሄ እንዳለው አንድ ቀን አባ ፍራንሷ ማርቆስን አማከርኳቸው።  "ቀላል ነው ልጄ" አሉኝ አባ፤ "ከዛሬ ጀምሮ ሙሉ የክርስትና ስምህን - ሣህለ ሥላሴ ብርሃነ ማርያም - ብለህ አስመዝግብ ሲሉ መከሩኝ"። ከዚያን ቀን ጀምሮ የልጅነት ስሜን ትቼ በክርስትና ስሜ እጠራ ጀመር።*

*በባህል ጫና ምክንያት የአገር ቤት ስሜን ትቼ በክርስትና ስሜ መጠራት የጀመርኩት እኔ ብቻ አይደለሁም። አብዛኛዎቹ ጓደኞቼ እንደኔው የአገር ቤት ስማቸውን ትተው በክርስትና ስማቸው ወይም ደሞ የአገር ቤት ስማቸውን ለወጥ አድርገው አማርኛ እንዲመስል ያደረጉም እንደነበሩ አስታውሳለሁ። ለምሳሌ ንጋቶ የነበረውን ንጋቱ፤ ዘልወት የነበረውን ዘነበች፤ ተስየ የነበረውን ተሰማ...እያሉ ጠምዘዝ በማድረግ አማርኛ እንዲመስል ያደረጉ አሉ፤* በማለት ያወጉናል ሣህለ ሥላሴ ብርሃነ ማርያም።

አዎ፤ ይህ የዘመኑ ጎምዛዝ እውነት ነው!

በኢትዮጵያ ታሪክ አባጣ ጎርባጣ ከሆነው የሁዋላ ዘመን ታሪካችን አንዱና ዋናው ይህ ደራሲ ሣህለ ሥላሴ ያጫወቱን የባህል ጫና ውጤት የሆነው የብሄረሰብ አባላት መጠሪያ ስሞችና የአካባቢያቸው መለያ አማርኛዊ እንዲሆኑ መደረጋቸው ወይም ግለሰቦች በስማቸው አማርኛዊ አለመሆን ሥነ ልቦናዊ ጫና እንዲያድርባቸው

መሆኑ ነበር። ይህንን እውነታ መካድም ሆነ ማድበስበስ ስህተቱ ትክክል ነበር ብሎ ማመን ይሆናል። እንዲህ የነበረው ሂደት እንኳንና የዚህ ዘመን ትውልድ የሁዋለኛውም ቢሆን ትክክል ነበር አይልም።

ከ1967 ዓ/ም የሥርዐት ለውጥ በፊት የኖረው ዘውዳዊ ሥርዐት የነበረውን ሀገራዊ የፖለቲካና የሶሺዮ ኢኮኖሚ የዕድገት ደረጃ፤ የህብረተሰቡንም ንቃተ ህሊና ደርዝ *በዋናነት ታሳቢና መነሻ በማድረግ* የዘመኑን ስህተት መመርመር ከቻልን መደምደሚያችን - ዛሬ በኢትዮጵያ የጎጥ ፖለቲካን ማራገብና በየስርቻውም የጎጥ ድርጅቶችን መፈልፈል ባልሆነ ነበር።

ምንም እንኳን ደርግ በሥልጣን ዘመኑ በፈፀመው ቁልል ሀገራዊ ወንጀል ምክንያት፤ የኢትዮጵያ ህዝብ ባቀጣጠለው አብዮት ያስመዘገባቸው ጭብጥ ድሎች ቢሸፈኑም ቅሉ፤ በተካሄደው ሥርዐተ ለውጥ ከተገኙት ድሎች አበይት የሆነው የኢትዮጵያ ብሄረሰቦች የየራሳቸው ቋንቋና ባህል መብት መረጋገጡና መከበሩ ነበር። ከአብዮቱ በፊት - እንደ ደራሲ ሣህለ ሥላሴ አገላለፅ የነበረው የባህል ጫና - ከአብዮቱ በሁዋላ በዘመነ ደርግ በገንቢ ጎኑ አልተለወጠም ብሎ የሚከራከር የሚክድም ካለ - እርሱ አንድም ህወሃታዊ አንድም ሻዕቢያዊ አንድም ኦነጋዊ...ቫይረስ የተጠናወተው፤ ቂም አርግዞ ቂም የሚዘራ ጎጠኛ ብቻ ነው። እርግጥ ነው በ1966ቱ አብዮት የተገኘው የብሄረሰቦች እኩልነት አቅጣጫውንና ዓላማውን ስቶ በህወሃት/ኢህአዴግ ዘመን ተቀልብሷል።...

ደርግ ህወሃትን የተዋጋው፤ ሻዕቢያን የተዋጋው፤ ኦነግን የተዋጋው...የብሄረሰብ ድርጅቶች ስለሆኑ፤ ኦሮምኛና ትግርኛ ስለሚናገሩ፤ አልነበረም። ታሪክን ሸረው፤ ሉዐላዊነትን ገስሰው፤ ሰንደቅ ዓላማን ረግጠው፤ ኢትዮጵያዊነታቸውን ክደው - የጎጥ መንግሥታትን ለመመስረት በመነሳታቸው እንጂ!...በዘውድ ሥርዐተ ዘመናት እንኳን ከቶም ያልታየና ያልነበረ አምባገነናዊ የዘር መድልዖ አገዛዝ የተመሰረተውና የተንሰራፋው ግን ህወሃት ሻዕቢያና ኦነግ የኢሕዲሪን መንግሥት ከጣሉ በሁዋላ ነው፤ ምንም እንኳን ኦነግ ዓላማው ባይሰምርለትም። ደርግ ሀገራዊ አምባገነን መንግሥት እንጂ አፓርታይዳዊ መንግሥት አልነበረም! ህወሃት/ኢህአዴግ ግን አምባገነናዊና አፓርታይዳዊ መንግሥት ነው። መራራው እውነት ይኸው ነው።

አንጋፋው ብዕረተኛ ሣህለ ሥላሴ ብርሃነ ማርያም በዛን ዘመን የነበረውን የባህል ጫና ይህም ያስከተለውን ቀውስ ከራሳቸው የህይወት ተሞክሮ በመነሳት ለታሪክ ያቀረቡበትን መንገድ ስናጤን የሰብዕናቸውን ታላቅነት ብቻ ሳይሆን የምንረዳው - የትውልድ፤ የታሪክ፤ የዜግነትና የሀገር ሃላፊነት በእጅጉ የሚሰማቸው መሆናቸውንም ጭምር ነው። የተባው ብእራቸው የነበረውን ታሪክ በታሪክ ሰነድነት ከማስቀመጥ፤ ስህተቱንም ከማሳየት ባሻገር - ይህ ትውልድ ባልኖረበትና በማያውቀው የዛን ዘመን 'የባህል ጫና' ብሄረሰባዊ ስሜቱን በመቀስቀስ በዘረኝነት ቂም በቀል ቫይረስ እንዲበከል የሚያመቻችና የሚመራ አንዳችም ጎጠኛ ሽንቁር በመፅሀፋቸው አልከፈቱም። ይልቁንም ስማቸው ሳይቀየር የመቅረቱን ሁነት ሲያነጥቡ፤ *...ከ1966 ዓ/ም አብዮት በሁዋላ...ጥቂት የማይባሉ ግለሰቦች በቀድሞው የአገር ቤት ስማቸው መጠራት ጀመሩ። እኔ ግን ሰነድ የያዘውን ስሜን ትቼ* ***ወደ ሁዋላ ለመመለስ ሳልፈቅድ ቀርቻለሁ፤*** ብለዋል።

ነገር ግን በተመሳሳይ ዘመን እንደ ደራሲ ሣህለ ሥላሴ በተመሳሳይ 'የባህል ጫና' ውስጥ ያለፉ፤ በተመሳሳይ ዘመን በኖረው መንግሥት ድጋፍና ክብካቤ የተማሩ የተመራመሩ በዛሬ ዘመን <ምሁራን፤ ልሂቃን> የሚል ቅፅል የቀፀሉ - ስለ ብሄረሰቦቻቸው 'ነፃነት' ዘብ ቆመናል እሚሉ፤ በሚፅፉት በሚናገሩት የቂመኛ የበቀለኛ የዘር መርዝ የሚረጩት፤ አልፎ ተርፎም የዋሁን ህዝብ በደም ሊያጥቡት በጎጥ ድርጅቶቻቸው የጦር ነጋሪት የሚጎስሙት/የጎሰሙት...ሣህለ ሥላሴን ከመሳሰሉት ጎን አቁመናቸው ስንመረምር፤ **እውነትም የእናት ሆድ ዥንጉርጉር!!**

ለመሆኑ 'የባህል ጫና' ሲነሳ ፈረንጅ ሀገርን ያሰበው ይኖር ይሆን? ኢትዮጵያዊው ምልዐተ ስደተኛ በየሚኖርበት ሀገር መጠሪያ ስሙ እንክትክት፤ ስብርብር፤ ውልግድግድ ያልተደረገበት ማን ነው? በየትኛው ሀገር ነው መጠሪያ ስማችን ከናባታችን ሳይቆራረጥ ሳይውገረገር ሲጠራ የሰማነው? በዚህ ምክንያትስ ስንቶቻችን የስነ ልቡና ጭንቀት አድሮብናል? ስንቶቻችን ስማችንን ከናባታችን አሳጥረነዋል? ቆርጠነዋል? ቀይረነዋል? እርግጥ ያስገደደን የለም። ስማችን የኛ ስም አልመስል ሲለን፤ ቃሉን ከናናባቢው፤ ከነድምፀቱ መጥራት - ሮኬት ሳይንስ ሲሆንባቸው - ከዚህ በላይ "የባህል ጫና" ከየት ይምጣ? ታዲያ ስማችንን መቀየር፤ ማሳጠር ወይም 'ዞር' (ለምሳሌ 'መላኩ'ን 'ማይክ') ማድረግ ይነሰን? እና እንግዲህ እኛም በፈረንጅ ሀገር "የባህል ጫና" ሰለባዎች መሆናችን ይሆን? **እንግዲህ የዚህን ትዝብት አንደምታ አንባቢ ይመርምር።** እኛ ግን ከዚህ በላይ ምንም አንል፤ ቅኝታችንን ግን እንቀጥል።

እነሆ ፍኖተ ሕይወት በደራሲው ሕይወት ጅረት እያንሳፈፈን፤ ትላንትን ከዛሬ፤ ዛሬን ከነገ እያንሰላሰልን እንድንቃኝ ይሞግተናል ይፈትነናል ያስተምረንማል። በእስካሁኑ ምልከታችን ሣህሌን እንጠይቅ ዘንዳ የሚገባን ጉዳይ አለን። ይህ ነው፤ ለመሆኑ ሣህሌ የክርስትና ስማቸውን እንዲጠቀሙ እንዴት ቢሆን ነው የውጪ ዜጋ

ስም ያላቸው <አባ ፍራንሷ> ምክር ሊለግሱ የቻሉት? ማንናቸው አባ ፍራንሷ? ፍኖተ ሕይወት በሰፊው አፍታትቶ ካወረደው የሚከተለውን ቀንጭበናል።

*አባ ፍራንሷ ማርቆስ የአምያ (ሰባት ቤት ጉራጌ) ተወላጅና የአባቴም የልብ ወዳጅ ናቸው። በእኔ ህይወት ላይ አሻራቸውን የጣሉና ሰባት ቤት ጉራጌንም ያስተማሩ ታላቅ መንፈሳዊ ሰውና ምሁር /ናቸው/...*

*አባ ፍራንሷ ማርቆስ አጭር፤ ወፍራም፤ ጠይም፤ ፊታቸው ላይ ዘወትር ፍልቅልቅታ የሚያሳዩ፤ ወንዱንም ሴቱንም <ልጄ> ብለው በአባታዊ ስሜት የሚጠሩ፤ ክረምት ሆነ በጋ ሰው ታሟል ካሏቸው ቅርብ ከሆነ በእግራቸው ሩቅ ከሆነ በሰጋር በቅሏቸው ተጉዘው የሚጠይቁ፤ በቆዳ ቦርሳቸው ይዘውት ከሚሄዱት ቴርሞሜትር (የሙቀት መለኪያ) ትኩሳት የሚለኩ፤ ኪኒን (የፈውስ መድሃኒት) በነፃ የሚያድሉ፤ በእየቦታው እየተዘዋወሩ ወላጆች ልጆቻቸውን እንዲያስተምሩ የሚመክሩና የሚገፋፉ፤ ለድሆች የሚራሩና ድሆችን የሚረዱ፤ በመላው ሰባት ቤት ጉራጌ በጣም የታወቁ፤ የተወደዱና የተከበሩ ሰው ነበሩ።...*

*...አባ ፍራንሷ ማርቆስ በርካታ ቋንቋ ተምረዋል። ፈረንሳይኛ እንደ ፈረንሳይኛ ተወላጅ ይናገራሉ፤ ይፅፋሉም። የላቲን ቋንቋ ያውቃሉ፤ ቅዳሴም የሚቀድሱት በላቲን ቋንቋ ነበረ። ሐረርጌ ውስጥ ስለኖሩ ይመስለኛል ኦሮምኛ ይናገራሉ። ጉራጊኛ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ሲሆን አማርኛ ደሞ ካፍ መፍቻ ቋንቋቸው በበለጠ ደረጃ ይናገራሉ፤ ይፅፋሉም። ሲሰብኩ አንደበተ ርቱዕ ናቸው፤ የአድማጫቸውን መንፈስ የመግዛት ሃይል አላቸው...*ይሉናል ሣህለ ሥላሴ አባ ፍራንሷን ሲያስተዋውቁን።

እነሆ አባ ፍራንሷ ማርቆስን በአካል ያገኘናቸው እስኪመስለን ትክለ ቁመናቸውን ስለን ተዋወቅናቸው። ፍራንሷ ይባሉ እንጂ ለካስ ኢትዮጵያዊ ናቸው፤ የሰባት ቤት ጉራጌ ተወላጅ። ህብረ ብሄር ቋንቋን - ጉራጊኛን ኦሮምኛን አማርኛን የሚያቀላጥፉ፤ በፈረንሳይ በግሪክ ልሳን የተጠበቡ...ያገር ምሁር የአምያ የኢትዮጵያ፤ አባ ፍራንሷ።

እንግዲህ በውስጣችን - የሰባት ቤት ጉራጌ ምሁሩ አባ ፍራንሷ ስማቸው ጉራጊኛም እንኳን ባይሆን አማርኛም አለመሆኑ 'የባህል ተፅዕኖ' ያመጣባቸው ወይስ የፈቃደኝነት  የዕምነት ክታብ? ብለን ብንጠይቅም፤ ለመልሱ ግን አንጨነቅም። ለምን? ቢሉ...ይህን ይመልሳሉ። አባ ፍራንሷ ኦሮሞ ናቸው። አባ ፍራንሷ አማራ ናቸው። አባ ፍራንሷ ጉራጌ ናቸው። አባ ፍራንሷ ኢትዮጵያዊ ናቸው። ይኸው ነው፤ በቃ!

**<u>5. ተፈሪ መኮንን ት/ቤት እና አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ</u>**

ፍኖተ ሕይወት ካካፈለን ከሰፊው ትውስታ መካከል የሚከተለውን በአርምሞ ያነቧል፤ *በተፈሪ መኮንን ት/ቤት በአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ እንማር በነበርንባቸው ዓመታት በከፍተኛ ጉጉት እንጠባበቅ የነበረው የገና በዓልን ስጦታ ነበር።...*

*የአዲስ አበባ ተማሪዎች በሙሉ በእየዓመቱ በገና በዓል ሰሞን ወደ ገነተ ልዑል ቤተ መንግሥት (የዛሬው አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ስድስት ኪሎ ካምፓስ) ሄደው ከጃንሆይ እጅ የገና ስጦታ ይቀበሉ ነበር። የተፈሪ መኮንን፤ የዊንጌት፤ የኮተቤ፤ የዳግማዊ ምኒልክና የሌሎችም የአዲስ አበባ ት/ቤቶች ተማሪዎች ከእየአቅጣጫው በሰልፍ ሆነው የኢትዮጵያ ባንዲራ ይዘው ወደዚያ ይጎርፋሉ።...*

*በእየዓመቱ የሚታደለው ስጦታ አንድ የገላ ሹራብ አንድ ውሃ የከበደው ብርቱካን አንድ ደሞ በጣም የሚጣፍጥ ባለዘቢብ ሙልሙል ብስኩት ነበር። የገላው ሹራብ ቀለሙ ከት/ቤት እት/ቤት ይለያይ ነበር።...ለመጀመሪያ ጊዜ ያገኘሁትን የገና ስጦታ ለአባቴ ዳዳ አናንቃ ያሳየሁዋቸው እለት እጅግ ደስ አላቸው። ጃንሆይ የሰጡኝ ስጦታ መሆኑን ስነግራቸው በታላቅ ግርምት <ከጃንሆይ ከራሳቸው እጅ ነው የተቀበልከው?> አሉኝ። <አዎን ከጃንሆይ ከራሳቸው እጅ!>*

*<እግዚር ያኽ ነረናኽ!> (እግዚኦ አንተ አለህ!) አሉ ለማመን በሚያስቸግር አድናቆት። ጃንሆይ የአገረ ገዢነት ወይም የሚኒስትርነት ሹመት ሰጡኝ ብላቸው ኖሮ ከዚህ በላይ ይደነቁ፤ ከዚህ በላይ ይደሰቱ ነበር ለማለት ይቸግረኛል...*በማለት አስፍረዋል ደራሲ ሣህለ ሥላሴ።

እውነት ነው፤ ምን ዳዳ አናንቃ ብቻ! እኛም በዚህ ዘመን ያለነው እንዲህ ያለ ታሪክ ስናነብና ስንሰማ ማመን እስኪያቅተን፤ ተረት እስኪመስለን ድረስ ያስደምመናል። በመሪና በተመሪ መካከል የነበረው "ሰዋዊ ግንኙነት" ያስቀናናል። ከጃንሆይ በሁዋላ የመጡትን መሪዎች ስንመዝንና ባለንበት ዘመን በእኛና በመሪዎቻችን ያለውን አፅናፋዊ እርቀት ስናስብ፤ የእኛ ዘመን ያስጠላናል። የሁዋላውን ዘመን መኖር ያምረናል። ወይ ዘመን አስብሎ ያስቆዝመናል...ወይ መሪ! ወይ ተመሪ! ወይ ነዶ!

እነሆም ባለፈው ዘመን መቆዘም ካልቀረልን ቀጣዩን ደግሞ እንጨምር። እንዲህ ያነቧል፤ *...ስለዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ህይወታችን ወደ ሁዋላ መለስ ብዬ ሳስብ ከሁሉ አስቀድሞ ከፊቴ የሚደቀነው ገና እዚያ ከመግባታችን በልካችን ተሰፍቶ **በነፃ** የሚታደለን ሙሉ ሱፍ  ልብስና በኮቱ ደረት ላይ የሚለጠፈው የዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ አርማ ነው። የኮቱ ቀለም ጥቁር ሰማያዊ፤ የሱሬው ደግሞ ዛጎልማ እንደነበርና አርማው ወርቃማ ቀለም እንደነበረው ትዝ ይለኛል። ያንን ዩኒፎርም ለብሶ አደባባይ መውጣት ከፍተኛ የሆነ የልብ ኩራት የሚያጎናፅፍ ነበር። **ሕብረተሰቡ ያንን ዩኒፎርም ለብሰን ሲያይ ራሱ ኩራት ይሰማዋል።** የአገሪቱ የወደፊት አመራር አካል ሊድርጎም ይቆጥረናል...ዩኒፎርሙን ለብሰን ከተልካሻ ቦታ ላይ አንሄድም፤ ተልካሻ ተግባርም አንፈፅምም። **ለዩኒፎርሙና ለተምሳሌነቱ የሚገባውን ክብር እንሰጥ ነበር፤*** ይሉናል ሣህሌ።

አወይ ዘመን፤ አወይ ጊዜ! ደረት መድቃት ይሄኔ። ሙሾ ማውረድ ይሄኔ። ለራስ ማዘን ይሄኔ። የኛስ ዘመን መጥኔ።

በእኛ ዘመን መንግሥትማ፤ በዘመነ ህወሃት - እንኳን የዩኒፎርም ተምሳሌነት ሊከበር  የኢትዮጵያ ባንዲራም ተዋርዷል። ኢትዮጵያዊነትን ማዜም ወንጀል ሆኗል። በእኛ ዘመን መንግሥትማ እንኳንና መማራችን ሊያስከብረን፤ ሰው የመሆናችን ዳርድንበራችን በገዛ ሀገራችን ተጥሷል፤ ዜግነታችን በገዛ ሀገራችን መሪዎች ትርጉምና ዋጋ አጥቷል። በእኛ ዘመን መንግሥትማ - በዘመነ ህወሃት፤ እንኳን ዲግሪ ጭነን በእውቀታችን ልንሰራ፤ ድንጋይ ፈለጣም ጥብስ ሆኖብናል። የእኛ ዘመን መሪዎችማ እንኳን ብርቱካንና ዘቢብ ብስኩት ሊያድሉን፤ ባቄላና በቆሎንም በነፃ ገበያ ቀምተውናል። የእኛ ዘመን መሪዎችማ እንኳን ቤተ መንግሥት ጠርተው ቤታቸውን ሊያስጎበኙን፤ ደሳሳ ጎጆዎቻችን በልማት ሰም አናታችን ላይ አፈራርሰው ከሰፈራችንም አባርረውናል። የእኛን ዘመን መሪዎችማ...ስንቱን ግፍ ቆጥረን እንዘልቃለን? ይልቅ እንመለስ ወደ ጥንቱ፤ ወደ ፍኖተ ሕይወት ትርክቱ። ሣህለ ሥላሴ እንዲህ ይላሉ፤

*...ሌላው ከአእምሮዬ የማይጠፋው የድሎት ኑሮው ነበር /በዩኒቨርሲቲ/። ምግብ እንደልብ ነው። ያውም ምርጥ የፈረንጅ ምግብ። ወተት እንደውሃ ከበርሜል ጋር በተያያዘ ቧንቧ እየቀዳን እንጠጣ እንደነበር አስታውሳለሁ። ፍራፍሬም በሽበሽ ነበር።*

*አልፎ አልፎ ንጉሠ ነገሥቱ በአንጋቾቻቸው ታጅበው ከምግብ ቤታችን ከቸች ይላሉ። ብርቱካን፤ ሙዝ፤ የወይን ዘለላ አስይዘው ይመጡና ይታደለናል።  **በምግብ ሰዓት በሚጎበኙን ጊዜ ከገበታችን እንኳን አንነሳም።** ምግብ ክቡር ነው ስለሚባል ይመስለኛል **መመገባችንን እንቀጥላለን እንጂ ተነስተን እጅ አንነሳም።** እሳቸው ግን ከአንዱ ጠረጴዛ ወደሌላው እየተረማመዱ ያነጋግሩናል። አንዳንድ ጥያቄ ይጠይቁናል። አንድ ቀን ሥጋ በመመገብ ላይ እያለን ቀረብ አሉኝና፤ <ለምንድን ነው ሥጋ የምትበላው?> አሉኝ። <ስለሚጣፍጠኝ> አልኳቸው። በሰጠሁዋቸው መልስ የተደሰቱ አልመሰለኝም። ፊታቸውን አዞረው ወደሌላው ባልደረባችን ሄድ ብለው <ለምንድን ነው ሥጋ የምትበላው?> ሲሉ ጠየቁት። <ካሎሪ ስላለው> አላቸው። በሳይንሳዊ መልሱ ተደስተው ነው መሰለኝ ፈገግ አሉለት፤* ሲሉ ያጫውቱናል አንጋፋው ደራሲ ሣህለ ሥላሴ ብርሃነ ማርያም።

ታዲያ እኛም ዛሬ ላይ ቆመን ይህንን ስናነብ - እንደ ጃንሆይ በሳይንሳዊ መልሱ ባይሆንም - በቃለ ምልልሱ ድራማዊነት ተመስጠን ፈገግ ብለናል።...እንደውም እንደ ህልም እያስለመለመ ወስዶን...ልጆቹን ለማስደሰት እንደሚጥር አባት፤ ሙዝና ብርቱካን አሸክመው በዚያ ተማሪ ትውልድ መኻል ጃንሆይ ከጠረጴዛ ጠረጴዛ ሲዘዋወሩ ይታዩናል።...<አባባ ጃንሆይ የቀለም አባት/ አሳድገውናል በማር በወተት> እየተባለ ይዘመር ነበር ሲሉም ሰምተናል። ይህ ከተዘመረም ሀሰትነት አልነበረውም፤ ቢያንስ ለዚያ ተማሪ። ወተት በቧንቧ፤ ክትፎ በጣባ ቀርቦላቸዋል - የዛሬ ዘመን አረጋውያን ልሂቃኑ፤ ውለው አድረው ሃይለ ሥላሴን <ሌባ> ያሉ፤ <ያልተገራ ፈረስ ጠቅል እያላችሁ/ ከማይጨው ፈርጥጦ ለንደን ገባላችሁ> ብለው የታሪክን ሀቅ አጣመው የገጠሙ ያዜሙና ያስዜሙ፤ ታሪክና መሪን የማዋረድን ፈር የቀደዱ...አዎ፤ ያ ትውልድ! ጡር ሳይኖርበት ይቀራል?!...ያሰኛል።

**<u>6. ባህር ማዶ</u>**

እነሆ በቤተ ጉራጌ በቸሃ ወረዳ በሲስ መንደር ዳዳ አናንቃ በሰንበሌጥ እየጠቆሙ <ሀ ሁ> ያስቆጠሩት ሣህሌ በ1951 ዓ/ም ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የመጀመሪያ ዲግሪውን ለማግኘት በቃ። የዕውቀት ጥማቱ ግን ገና አልረካም። በዘመኑ ወደ ውጪ ሀገር ሄደው ትምህርታቸውን መቀጠል ለሚፈልጉ የዩኒቨርሲቲው ምሩቃን የኢትዮጵያ መንግሥት የስኮላርሺፕ እድል ይሰጥ ነበር። ይህንን አስመልክቶ ፍኖተ ሕይወት ሲያወጋን፤ *...ሳይንስ፤ የማስተማር ሙያ፤ ኢኮኖሚክስ የመሳሰሉትን ትምህርት ለማጥናት ያመለከቱ ጓደኞቻችን የኢትዮጵያ መንግሥት ስኮላርሺፕ ሲያገኙ እኔና ሌሎች ባልደረቦቼ (ፖለቲካል ሳይንስ ወይም ሥነ መንግሥት ለማጥናት ያመለከትነው) ጥያቄአችን ውድቅ ሆነብን...*ይላሉ ደራሲው።

በዚህ ትረካ ሁለት አቢይ ነጥቦችን እንገነዘባለን። የኢትዮጵያ መንግሥት ትምህርታቸውን በከፍተኛ ደረጃ እንዲከታተሉ ስኮላርሺፕ የሚያዘጋጀው፤ በጤና፤ በኢኮኖሚክስ፤ በሳይንስ፤ በማኔጅመንትና በመሳሰሉት የሙያ ዘርፎች ሠልጥነው ወደ ሀገራቸው በመመለስ ሊያገለግሉ እንዲችሉ መሆኑ አንደኛው ሲሆን፤ ከዚህ በተቃራኒ የፖለቲካ ሳይንስና ሥነ መንግሥት የመሳሰሉ ለከፍተኛ ደረጃ የሚያዘጋጁ ትምህርቶችን ስኮላርሲፕ እንደማይሰጥ መሆኑ ነው። ሙያዊ ዕውቀትንና "መንግሥታዊ" እውቀትን ለይቶ ማስመሩ።

መቼም እኛ ጥንታውያን ሲተርቱ <ወፍ እንደ ሀገሯ ትዘፍናለች> ይላሉ። በዘመኑ ለኖረው የጃንሆይ መንግሥት - የፖለቲካ ሳይንስም ሆነ ሥነ መንግሥት - በሚል በሁለተኛ ዲግሪ ወይም በዶክትሬት የሚያስመርቅ የትምህርት ስኮላርሺፕ፤ ቅኝቱም ሆነ ዜማው ለሥርዐተ መንግሥቱ አይስማማውምና አላዜመውም። ወደዚያም የሚያመራን መንገድ አልፈቀደም። የዘመኑ መንግሥት ይህን ለምን አደረገ ብለን በዛሬ ዘመን መነፅር ልንዳኘው ይቻለናልን? የሞራል ብቃቱስ አለን ይሆን?

ደራሲ ሣህለ ሥላሴ በተባው ብዕራቸው ታሪክንና የክስተትን ሂደት በማንሰላሰል ባልጎመዘዘ፤ ባልመረረ፤ ባላማረረ ውብ የሥነ ፅሁፍ ማዕዳቸው የዚያን ዘመኑን ታሪክ መገቡን እንጂ - የጃንሆይን መንግሥት አልፈረጁትም። በነገርም አልፈጁትም።

የኢትዮጵያ መንግሥት የፍላጎታቸውን ስኮላርሺፕ ቢነፍጋቸውም እነ ሣህሌ በፈረንሳይ ኤምባሲ በኩል ሌላ ስኮላርሺፕ ማግኘት ችለው ነበር። ፍኖተ ሕይወት የውጪ ሀገሩን ጉዞ አስመልክቶ እንዲህ ይላል፤ *የኢትዮጵያ መንግሥት ምንም እንኳን ፖለቲካል ሳይንስ ለማጥናት ለፈለግነው እስኮላርሺፕ ቢነፍገንም ለሌሎች እንደሚያደርገው ሁሉ ለእኛም አንድ አንድ ሙሉ ልብስ (ሱፍ) እንደገዛልንና እኛም የአገር ልብስ (እጀ ጠባብ፤ ተፈሪ ቅድ ሱሪ እና ባለጥበብ ነጠላ) ገዝተን እንድንሄድ እንደመከረን አስታውሳለሁ። ለትምህርት ወደ ውጪ ሀገር የሚሄዱ ተማሪዎች አምባሳደሮች ባይሆኑም በግላቸው* ***ኢትዮጵያን እንደሚወክሉ ሆኖ ይቆጠር ስለነበር*** *መንግሥት ጠባያችንን እንድናሳምር፤ የኢትዮጵያን ስም በክፉ እንዳናስጠራ ይመክረን ነበር፤* ይሉናል ሣህለ ሥላሴ ትውስታቸውን ሲያወጉን።

መቼም ጊዜ አያመጣው፤ ጊዜ አያሳየውም የለ - እድሜ ካለ። በዚያን ዘመን የነበሩት መሪዎች፤ ነገሥታቱ - ወደ ውጪ ሀገር የሚሄዱ ኢትዮጵያውያንን እንደ ሀገር ወኪል፤ እንዳምባሳደር ያህል ይቆጥሩዋቸው ነበርና - ራሳቸውን ጠብቀውና አስከብረው ሀገራቸውንም እንዲያስከብሩ ይመክራሉ፤ ለችግራቸውም ደራሾች ነበሩ። በዚህ ዘመን፤ ህወሃት በሚመራው መንግሥት - በውጪ ሀገር የተሰደዱ ኢትዮጵያውያን ሀገር እንደሌላቸው እንዲሰማቸው የሚደረግበት፤ ኢትዮጵያዊነትም (በሀገር ውስጥ ጭምር) መንፈሱና እምነቱ በመንግሥት ደረጃ የተዋረደበትና የዘር ሀረግ የገነነበት በመሆኑ - ለምሳሌ በአረብ ምድር በተለይም በሳኡዲ አረቢያ <የመንግሥት ያለህ፤ የሀገር ያለህ! ተዋርደናል፤ ሞተናል፤ በጋጠወጥ አረቦች ሴቶች እህቶቻችን ተደፍረዋል፤ ወንዶች በየአደባባዩ ተገድለዋል> በማለት አቤት ብለው ጥሪ ያቀረቡትን በሺህ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያንን ድምፅ የሚሰማ፤ ጥቃታቸውንም የሚከላከልና የሚመክት የሀገርና የዜጋን ክብር የሚያስከብር ደራሽ መንግሥት ሊሆን አልቻለም። ሀገር እያላቸው ወፍ ዘራሽ የሆኑ ይመስል፤ በሀገራቸውም መንበር ላይ የተቀመጠ መንግሥት እያለ መንግሥት የማያውቃቸው የውጪ ዜጎች የሆኑ ይመስል የጣዕረ ሞት ጩኸታቸው ለህወሃት መንግሥት እንደ በረኻ ጩኸት ሆኗል፤ የማይሰማ።

በዚህ ዘመን መንግሥት፤ በዘመነ ህወሃት - በውጪ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እንደ ሀገር አምባሳደር ሊቆጠሩ ቀርቶ - በሊባኖስ፤ በግብፅ ከሁሉም በላይ ደግሞ በሳዑዲ የሚገኙ ስደተኛ ኢትዮጵያውያን - በታሪክ ታይቶና ተሰምቶ በማያውቅ ሁኔታ ለሞት፤ ለአስገድዶ መደፈር፤ ለዘግናኝ ድብደባና እስር ከመዳረጋቸው በፊት - በዓለም ሀገራት መድረክ ኢትዮጵያውያን የሚታወቁት - ጨዋ፤ ትሁት፤ ኩሩና አትንኩኝ ባይ ህዝብ - በመሆናቸው ነበር። የቀድሞው ዘመን መንግሥታት - በተለይም ጃንሆይና ከሳቸውም በፊት የነበሩት ነገሥታት - በታላቅ ትዕግስትና ዘዴ በዓለም ህብረተሰብ ልቡና ሲገነቡት የኖሩት የኢትዮጵያ መለያና ክብር ፀረ ኢትዮጵያ በሆነው የህወሃት መንግሥት እንደምን እንደተዋረደ በሳዑዲ የተካሄደው ፀረ ኢትዮጵያውያን ጭፍጨፋና ሰቆቃ ምስክር ነው።

ለጊዜው ይህንን ለጊዜ ሰጥተን እንመለስ ወደ ቅኝታችን። ደራሲ ሣህለ ሥላሴ ብርሃነ ማርያም ለትምህርት ወደ አውሮፓ ዘልቀው በተለያዩ ሀገራት ስላደረጉዋቸው ጉብኝቶች፤ በፈረንሳይ ሁዋላም በሀገረ አሜሪካ ስላሳለፉት የትምህርት ዘመናት ገጠመኞቻቸውን በየፈርጁ እያዋዙ በፍኖተ ሕይወት ውስጥ ናኝተዋል። ስሜት ኮርኳሪ፤ ልብ አሟቂ ትውስታዎች። እነሆ አብነት፤

*በዛንሶ /ፈረንሳይ/ በቆየንባቸው ጊዜአት ሌላው ተደናቂ ሆኖ የተገኘው የእኛው የአገር ልብስ ሆነ። እንደ በረዶ የነጣ ተፈሪ ቅድ ሱሪያችንን፤ መብሩቅ እጀ ጠባባችንን አጥልቀን በጥበብ የተጌጠውን ነጠላችንን*

*አጣፍተን ለብሰን ባቡር መንገድ ላይ ብቅ በምንልበት ጊዜ ከዚያም ከዚህም ፈረንሳዮች እየከበቡን <ከወዴት አገር ናችሁ? ልብሳችሁ እንዴት ያምራል?> ሲሉን ልባችን በኩራት ያብጥ ነበር። ወደዚያ ከመሄዳችን በፊት መንግሥት ያገር ልብስ ይዘን እንድንሄድ የመከረን ለካስ ያለምክንያት አልነበረም። ያለጥርጥር ቢያንስ ከአዩን ፈረንሳውያን ጋር  አገራችንን ለማስተዋወቅ ችለናል። የአገር ልብሳችንን በተገቢው ደረጃ ባንይዘውም የውጪዎቹ በጣም እንደሚያደንቁት በተጨባጭ አይተናል፤* ሲሉ ያወሳሉ።

አዎ፤ እውነት ነው። እኒያ ጥንታውያን መሪዎች ኢትዮጵያን ለማስተዋወቅ፤ ኢትዮጵያውያንም በዓለም ህብረተሰብ ተገቢውን ስፍራ እንዲያገኙ ለማድረግ ዘመን የፈቀደላቸውን ያህል ደክመዋል። ፍሬውም ታይቷል፤ እነ ሣህሌ ምስክር ናቸውና። እንደ እውነቱ ከሆነ በኢትዮጵያ ታሪክ  እስከ 1983 ዓ/ም ድረስ በኢትዮጵያ መንበር ላይ የተቀመጡት መሪዎች - ሀገራዊ ህልውናን ወይም ሉአላዊነትን፤ ባንዲራንና ኢትዮጵያዊነትን - አስመልክቶ ከማንም በምንም ሳይደራደሩ ኖረዋል። ሉአላዊነት፤ ባንዲራና ኢትዮጵያዊነት - ለውይይት ወይም ሰጥቶ ለመቀበል ወይም ለሥላጣን ማሰንበቻ መደራደሪያነት- በኢትዮጵያ ታሪክ ቀርበው አያውቁም፤ እስከ ህወሃት ዘመነ መንግስት ድረስ። ቀደምት መንግሥታት የሀገርን ባህል፤ ቅርስና ህብረ ብሄር ውበትና አንድነት በማስተዋወቅ ረገድ - ራሱ ደርግ ሳይቀር ተረባርበዋል። ለምሳሌ ደርግ - "ህዝብ ለህዝብ" በሚል ፕሮግራም በመላው ዓለም ያካሄደውን ታላቅና ድንቅ ኢትዮጵያን የማስተዋወቅ ዘመቻ ያስታውሷል። ከዚህ አንፃር ለመሆኑ በህወሃት/ኢህአዴግ ዘመን ምን ተደርጓል?!...

# ክፍል ሁለት

## 2.1. *ሥነ ፅሁፍ* - የህይወት ተልዕኮ

### 7. ደራሲ ተርጓሚና ሃያሲ

*ሀ. ደራሲ፤* ሣህለ ሥላሴ ብርሃነ ማርያም ሥነ ፅሁፍ የህይወታቸው ተልዕኮ ሆኖ - በሥነ ፅሁፍ ለሥነ ፅሁፍ መኖር ከመጀመራቸው አስቀድሞ እንደምን ከሥነ ፅሁፍ አምባ ዘለቁ? ዘልቀውስ እንደምን ቤተኛ መሆን ቻሉ? ብዙዎች ከሥነ ፅሁፍ አምባ ወርደው፤ ከሥነ ፅሁፍ ቆሌ ከሥነ ፅሁፍ አድባር ምርቃት አጥተው፤ በአምባው ህልው ተማርረው፤ አምባውን 'መምሰል' እንጂ መሆን ተስነው...እርም ብእር ብለው ወጥተዋል። የብእር ምስ የብእር ፍዳ፤ የብእር ጣእር የብእር ጥሪ - የነፍስያ የውስጠ ውስጠት እንጂ፤ አይደለምና የጣት ኬሚስትሪ። ደራሲና ሥነ ፅሁፍ ሲፈታጣጠሙ - የህይወት ተልዕኮ ቃል ኪዳን ሲገባቡ፤ ህቅታ - የነፍስያ ማታ፤ እንጂ የሚለያቸው፤ አይደለም የህይወት ዘመን ፍዳቸው። ታዲያ እንደምን ሣህሌና ሥነ ፅሁፍ ተፈጣጥመው በአምባው ኖሩ? ኖረውም አፈሩ?...

እነሆ ፍኖተ ሕይወትን እናቀርባለን። ሣህሌ በፈረንሳይ 'ኤክስ አን ፕሮቫንስ' ውስጥ በተማሪነት ዘመናቸው ስለገጠማቸው <አይን ገላጭ> ክስተት ሲያወጉን እንዲህ ይላሉ፤ *...ሚሼል የሥነ ፅሁፍ ተማሪ ነች።...የሥነ ፅሁፍ ተማሪ እንደመሆኗ መጠን የማወቅ ፍላጎት አድሮባት አንድ ቀን <በዓለም የታወቁ ኢትዮጵያውያን ደራሲያን አሏችሁ?> ስትል ጠየቀችኝ። ጭንቅላቴ ላይ ቦንብ ያፈነዳችብኝ መሰለኝ። ስለዚህ ጉዳይ ከዚህ በፊት አስቤበት አላውቅም። በዓለም የታወቁ ስትል እንደ ቪክቶር ሁጎ፤ ዣን ፖል ሳርተር፤ አኖሬ ደ ባልዛክ፤ ዣን ዣክ ሩሶ፤ ማርሴል ፕሩስት፤ አንድሬ ሞርዋ፤ አንድሬ ዢድ፤ ከፈረንሳይም ውጪ እንደ ሼክስፒር፤ ቻርልስ ዲከንስ፤ ሊዮ ቶልስቶይ፤ ፊዮዶር ደስትየቪስኪ፤ ፑሽኪን፤ ኸርማን መልቪል እና የመሳሰሉትን ማለቷ እንደሆን ገብቶኛል። ነገር ግን በዚያን ጊዜ በዓለም ደረጃ ቀርቶ በአገር ዓቀፍ ደረጃም ቢሆን <ታላቅ> ተብለው ሊጠሩ የሚችሉ ስንት ኢትዮጵያውያን ደራሲያን ነበሩ? ከበደ ሚካኤል? አዎን። አፈወርቅ ገብረ ኢየሱስ? አዎን። ብላቴን ጌታ ህሩይ ወልደ ሥላሴ? አዎን። ከእነዚህ ውጪ ግን የማስታውሰው አልነበረም። እነሱም ቢሆኑ ሥራዎቻቸው ወደ ፈረንሳይኛ ወይም ወደ እንግሊዝኛ አለዚያም ወደ ሌሎች አበይት የዓለም ቋንቋዎች ያልተተረጎሙ በመሆናቸው ከኢትዮጵያ ውጪ የሚያውቃቸው የለም። እፍረት እየተሰማኝ <የእኛ ደራሲያን ሥራዎቻቸው ወደ አውሮፓ ቋንቋዎች ስላልተተረጎሙ እምብዛም አይታወቁም> ስል ሸፈንፈን አድርጌ መለስኩላት። ይህ ጥያቄዋ ግን ስለ ኢትዮጵያ ሥነ ፅሁፍ አንዳች ሀሳብ ሳይጭርብኝ አላለፈም። ኢትዮጵያ ከጥንታውያን አገሮች አንዷ ናት፤ የራሷ ፊደልና ጥንታዊ ሥልጣኔ አላት፤ እያልን እንዘፍናለን። ሥነ ፅሁፋችንን ከውጪዎቹ ሥነ ፅሁፍ ጋር ስናነፃፅር ግን ቤታችን ከባዶነት ያልራቀ መሆኑን እንገነዘባለን፤* በማለት አንጥበዋል።

አዎ እውነት ነው። ኢትዮጵያ ጥንታዊ ሥልጣኔ የነበራት ለመሆኑ በታሪክም ሆነ በአርኪዮሎጂ ግኝቶች የተረጋገጠ ቢሆንም፤ ያ! ሥልጣኔዋ በዘመንና በትውልድ ሂደት አብሯት አድጎ ትሩፋቱ በእድገቷና በሥልጣኔዋ ላይ ዘልቆ አልታየም። እርግጥ ነው ኢትዮጵያ ጥንታዊ የፅሁፍ ፊደል ያላት ሀገር ናት። ይህ ጥንታዊ የፅሁፍ

ፊደል ባለቤትነቷ በዘመናትና በትውልድ ሂደት ከእድሜው ጋር ተቀራራቢ የሆነ የሥነ ፅሁፍ በረከቶችን አላኖረም። ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ? ለጥያቄው ይህ ቅኝት ምላሽ ሊያቀብል አይቻለውም። ስለምን? ቢሉ - የመነሻችን ጭብጥ የቅኝታችንም ዳርቻ አለመሆኑ ብቻ ሳይሆን ርእሰ ጉዳዩ ሰፊና ጠሊቅ ትንታኔንም ይሻልና ነው። ግና በነቁጡ ዙሪያ የጥያቄው መነሳት ፋይዳው አንባቢን ለተጨማሪ ግለ ንባብ ለመኮርኮር ይችላል ከሚል እሳቤ ነው።

ሣህለ ሥላሴ በ1950ዎቹ ዓ/ም መግቢያ በሀገረ ፈረንሳይ ወጣቷ ሚሼል የሰነዘረችላቸው ጥያቄ የቦንብ ፍንዳታ ያህል ውስጣቸውን ያናጠው ምክንያቱ በኢትዮጵያ ጥንታዊ ታሪክና በነባራዊው እውነታ መኻል ያለው ገደል ክፍተት ድንገት ግዘፍ ነስቶ ስላፈጠጠባቸው ነበር። በዘመኑ የኢትዮጵያን ሥነ ፅሁፍ ውጤቶች ከውጪው ሀገራት ሥራዎች አንፃር በማመዛዘናቸውም ነበር <ሥነ ፅሁፋችንን ከውጪዎቹ ሥነ ፅሁፍ ጋር ስናነፃፅር ቤታችን ከባዶነት ያልራቀ መሆኑን እንገነዘባለን> ማለታቸው።

እነሆ የያኔው ወጣት ሣህለ ሥላሴ የሚሼል ፈንጂ በውስጡ እንደተቀበረ ወደ ሀገረ አሜሪካ በዚያው ዘመን አቀና፤ የፖለቲካል ሳይንስ ትምህርቱን በማስተርስ ዲግሪ ሊያጠና። በዚያም ከፕሮፌሰር ውልፍ ሌስሎው ጋር ተገናኘ። ፕሮፌሰር ውልፍ ሌስሎው የሰባት ቤት ጉራጌ ምሁርና የመንፈስ አባት የሆኑት የታላቁ አባ ፍራንሷ ማርቆስ የቅርብ ወዳጅ ናቸው። ሣህሌ ፕሮፌሰር ውልፍን የሚያውቃቸው በእምድብር ቀዳማዊ ሃይለ ሥላሴ አንደኛ ደራጃ ት/ቤት ተማሪ በነበረበት ወቅት ነበር። በዩኒቨርሲቲው መምህር የሆኑት ፕሮፌሰር ውልፍ ሌስሎው እነሆም የወጣቱን መፃኢ ጎዳና <አስቀያሽ> የሆነ ተልዕኮ ሰጡት። ፍኖተ ሕይወትን ያቀርቧል፤

*ሎስ አንጀለስ ያለነው የኢትዮጵያ ተማሪዎች መደበኛ ትምህርታችንን እየተከታተልን ከትምህርት ሰዓት ውጪ ከፕሮፌሰር ውልፍ ሌስሎው ጋር የምናሳልፈው ጊዜ ትንሽ አልነበረም። ፕሮፌሰር ሌስሎው ሰርተው የማይጠግቡ የሥነ ልሳን ሊቅ ናቸው። ፕሮፌሰር ሌስሎው ሴማዊ ቋንቋ ተናጋሪ የሆንነውን የኢትዮጵያ ተማሪዎች አንድ በአንድ እየጠሩን የቃላት ፍቺ፤ አጠራራቸውን ጭምር ይጠይቁናል። ዓላማቸው ከብዙ ዓመታት ድካም በሁዋላ የአማርኛ፤ የትግርኛ፤ የጉራጊኛ፤ የአደሪኛና የሌሎችም የኢትዮጵያ ሴማዊ ቋንቋዎች መዝገበ ቃላት አሳትመው ለማዘጋጀት ነው።...*

*እኔን የሚፈልጉኝ በጉራጊኛ ቋንቋ ለሚያካሂዱት ጥናት በተለይም ለቸሃኛው ቀበልኛ ነበር።...ይህንኑ በምናደርግበት ጊዜ አንድ ቀን <ለምን በጉራጊኛ ቋንቋ አንድ ዐይነት ፅሁፍ አታዘጋጅልኝም?> አሉኝ። <ምን ዐይነት ፅሁፍ?> አልኳቸው። <ስለ ገጠር ህይወት የሆነ ፅሁፍ ብታዘጋጅልኝ ደስ ይለኛል። በእየቀኑ አንድ ወይም ሁለት ገፅ ብትፅፍ ከተወሰነ ጊዜ በሁዋላ ጠርቀም ያለ ነገር ልታዘጋጅ ትችላለህ> አሉኝ።...*

*ፕሮፌሰር ሌስሎው እንደጠቆሙኝ በእየቀኑ አንድ ሁለት ገፅ እየፃፍኩ በሁለት ወር ውስጥ ከሰማኒያ ገፅ በላይ ያለው ፅሁፍ አዘጋጅቼ አቀረብኩላቸው። ፅሁፌን ከአዩት በሁዋላ እጅግ ደስ አላቸው። እንደቀልድም <ኢትዮጵያዊው ሄምንግዌ ልትሆን ነዋ!> የሚል ቃል ጣል አደረጉብኝ፤ ከፈገግታ ጋር።...*ይላል የፍኖተ ሕይወት ትውስታ።

እነሆ የፖለቲካል ሳይንስ ተማሪው ሣህለ ሥላሴ በፕሮፌሰር ሌስሎው አማካይነት ወደ ፈጠራ ሥራ፤ ሥነ ፅሁፍ አምባ - ገባ። ወጣቱ ሣህለ ሥላሴ ለፕሮፌሰር ሌስሎው ያዘጋጀው ፅሁፍ "የሺንጋ ቃያ" ይባላል። ይህ የሣህለ ሥላሴ የመጀመሪያ ሥራ በ1956 ዓ/ም ወደ እንግሊዝኛ ተተርጉሞ በዩኒቨርሲቲው የህትመት ክፍል በመፅሀፍ ታተመ፤ የሥነ ፅሁፍ 'ህሌታ' ተጀመረ? ፍኖተ ሕይወት እንዲህ ይላል፤ *...ሳላውቀውና ሳላስበው የአንድ መለስተኛ 'ልብ ወለድ' ደራሲ መሆኔን ተገነዘብኩ።...ወደፊት እቀጥልበት እንደሆን በዚያን ጊዜ ባልረዳም በዚህ ሁኔታ በአጋጣሚና በፕሮፌሰር ሌስሎው አነሳሽነት ከድርሰት ዓለም ውስጥ ገባሁ።* በማለት የድርሰት 'ህሌታ' ስለጀመሩበት ሥራ ያወጉናል ሣህለ ሥላሴ።

እሰየው! እንኳንም ወጣቱ ሣህሌ ከድርሰት ዓለም፤ ከሥነ ፅሁፍ አምባ - ገባ...

ከድርሰት ዓለም የገባው ወጣቱ ሣህሌ በድርሰት ዓለም በድርሰት አምባ አድጎ፤ በድርሰት አድባር የደራሲነት ብራኬን ለማግኘት ያለመታከት በብዕር ምሷል፤ ጎልጉሷል፤ ወቅቷል፤ አበራይቷል፤ አምርቷል። የማያባራውን የብዕር ማሳ፤ የብዕር እርሻ ድካሙን ውጣ ውረዱን ፍኖተ ሕይወት በስፋት አውርዷል፤ ዝርዝሩን አንባቢ ከማሳው ያጭድ ዘንድ ይቻለዋል።

እነሆ ከሺንጋዝ ቀዬ መታተም በሁዋላ በተለይም ደግሞ ዘ አፈርሳት፤ ዋርየር ኪንግ እና ፋየር ብራንድ የተሰኙት የእንግሊዝኛ መፃህፍትን በተከታታይ መውጣት ስንመለከት፤ ሚሼል ወጣቷ - ፈረንሳይቷ - ሣህሌን የጠየቀችው ጥያቄ በእዝነ ህሊናችን ዳግም ሲያስተጋባ ይሰማናል። እና ሚሼል እኒህን የእንግሊዝኛ መፃህፍት የማንበብ እድሉ አጋጥሟት ይሆን? ከሆነስ ምን ተሰምቷት ይሆን? እንላለን፤ በህሊናችን።

**ለ. ተርጓሚ፤** በኢትዮጵያ ሥነ ፅሁፍ ታሪክ የትርጉም ስራዎች ጉልህ አስተዋፅዖ አድርገዋል፤ በማድረግም ላይ ናቸው። የትርጉም ስራ ሀገራዊ እሴትነቱ ከሥነ ፅሁፍ ባሻገር በታሪክ፤ በፖቲካ፤ በኢኮኖሚና በማህበራዊ ሳይንስ ረገድም በውጪ ሀገር ቋንቋ ስለ ኢትዮጵያ የተፃፋትንና ወይም ለኢትዮጵያ ማህበረሰብ ተልእኮ ያላቸውን የትርጉም ስራዎች ጭምር ያጠቃልላል።

የትርጉም ስራን ሁለንተናዊ ወይም ሀገራዊ ፍሬ አስመልክቶ ደራሲ አያልነህ ሙላቱ በ1977 ዓ/ም <የሥነ ፅሁፍ ቅኝት> በሚል ባሳተሙት ሰፊ መፅሀፋቸው ሲያነጥቡ፤ *...ወደ አማርኛ የተተረጎሙት የውጪ ሀገር ሥነ ፅሁፎች በኢትዮጵያ ሥነ ፅሁፍ ላይ ይህ ነው የማይባል መሻሻልን አምጥተዋል። የሼክስፒርና የጎይቴ ስራዎች፤ የኤዞፕ ተረቶች፤ የራስ ሴላስ፤ የታላቁ እስክንድርና የማህተመ ጋንዲ ታሪኮች...ወደ አማርኛ ቋንቋ መተርጎም የሥነ ፅሁፋችን ይዘት ከምላ ጎደል እየተለወጠ እንዲመጣ አመቺ ሁኔታን ፈጥሯል...*ብለዋል።

እርግጥ ነው ዘመናዊው የኢትዮጵያ ሥነ ፅሁፍ (ልብ ወለድና ኢልብ ወለድ) ከ19መቶዎቹ ወዲህ እያደገና እየሰፋ የመጣ ሲሆን የዛሬው ዘመን ትውልድ ለደረሰበት የሥነ ፅሁፍ የእድገት ደረጃ ቋጥኝ አስተዋፅኦ ያበረከቱት አያሌ ፀሀፍትም ሊታሰቡና ሊዘከሩ ይገባል።

ግዕዝን የተካው የአማርኛ ሥነ ፅሁፍ መሰረት የተጣለው በአፄ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግሥት ለመሆኑ የኢትዮጵያን ሥነ ፅሁፍ እድገት ያጠኑ ጠቢባን ይስማማሉ። የመጀመሪያዎቹም የአማርኛ ፀሀፍት አለቃ ዘነብና አለቃ ወልደ ማርያም ናቸው። አፈወርቅ ገብረ ኢየሱስ የአማርኛን ሥነ ፅሁፍ መሰረት ከእነ አለቃ ዘነብ ተረክበው በዘመናዊ መልክ አቅርበዋል ይላሉ ጠበብቱ። ከዚህ በሁዋላ የኢትዮጵያ ሥነ ፅሁፍ እንደ ጅረት መፍሰስ ጀመረ፤ በተለይም ከሁለተኛው የጣሊያን ወረራ ወዲህ። በትውልድ ለዳበረው ጅረት ፍሰት ዘላቂነት የብእራቸውን ጭማቂ ከምንጩ አኑረው ካለፉት ጥቂቱ-መርሴ ሀዘን ወልደ ቂርቆስ፤ ገብረ ህይወት ባይከዳኝ፤ ተክለ ሃዋርያት ተክለ ማርያም፤ ህሩይ ወልደ ሥላሴ፤ ዮፍታሄ ንጉሴ፤  ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ፤ ይልማ ዴሬሳ፤ ብርሃኑ ዲንቃ፤ ከበደ ሚካኤል፤ ተክለ ፃድቅ መኩሪያ፤ መኮንን እንዳልካቸው፤ ግርማቸው ተክለ ሃዋርያት፤ እምሩ ሃይለ ሥላሴ፤ ማህተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል፤  አቤ ጎበኛ፤ ሲራክ ወልደ ሥላሴ፤ ደስታ ተክለ ወልድ፤ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፤ ሀዲስ ዓለማየሁ፤ መንግሥቱ ለማ፤ ጳውሎስ ኞኞ፤ አፈወርቅ ዮሐንስ፤ ማሞ ውድነህ፤ ብርሃኑ ዘሪሁን፤ በዓሉ ግርማ፤ ፀጋዬ ገብረ መድህን፤ ...እና ስማቸውን በዚህ ቅንጭብ መዘክር መዘርዘር ከቶም የማይቻለው ደራሲያን /ልብ ወለድም ሆነ ኢልብ ወለድ/ እና ተርጓሚያን የኢትዮጵያ ሥነ ፅሁፍ ዛሬ ለደረሰበት የደለበ ክምችትና ዕድገት ያበረከቱት ግዙፍ አስተዋፅኦ በእጅጉ ሊያስመሰግናቸው ብቻም ሳይሆን  በአግባቡም ሊዘከሩ  ይገባል፤ የኢትዮጵያ ሥነ ፅሁፍ ታሪክ አካልና ባለውለታ ናቸውና!

በእኒህና ባልተጠቀሱት አያሌ የኢትዮጵያ ሥነ ፅሁፍ ታሪክ ባለውለተኞች መሰረት ላይ የኢትዮጵያን ሥነ ፅሁፍ ከዘመንና ከትውልድ ጋር ወደፊት በማራመድ ረገድ የራስ የሆኑ ሥራዎችን (ልብ ወለድም ሆነ ኢልብ ወለድ) በማበርከትና አያሌ የውጪ ሥነ ፅሁፍ በረከቶችንም በመተርጎም - የኢትዮጵያን ሥነ ፅሁፍ ጎተራ በማድለብ ላይ የሚገኙት ወጣትና አንጋፋ ደራሲያን የኢትዮጵያ ሥነ ፅሁፍ ታሪክ አካል ናቸው፤ ውለተኞችም። እኒህንም በአግባቡ መያዝ፤ ወጣት ደራሲያንን ማበረታታት፤ አንጋፋዎቹንም ተገቢውን ቦታ መስጠትና መዘከር የትውልድና የሀገር ሃላፊነት ሊሆን ይገባ ነበር። ይህ በሥነ ፅሁፍ ብቻ ሳይሆን በተለያዩ የሙያ ዘርፎች ተሰልፈው ለሀገርና ለወገን አኩሪ ተግባርና ግልጋሎት የሰጡትን ብርቅዬ ኢትዮጵያውያንንም ያካትታል። ይሁንና በእስከ ዛሬ ታሪካችን ይህ ሲሆን አልታየም።

እነሆ እንግዲህ ሣህለ ሣላሴ ብርሃነ ማርያም  ከእኒህ መኻል አንዱ ባለ ታሪክ ሆነው ይገኛሉ። ደራሲ ሣህለ ስላሴ ወደ ትርጉም ዓለም የገቡት የመጀመሪያ መታያቸው በሆነው በ1975 ዓ/ም ባሳተሙት የእንግሊዛዊው ደራሲ ቻርልስ ዲከንስ <ኤ ቴል ኦፍ ቱ ሲቲስ> “የሁለት ከተሞች ወግ” በሚለው የትርጉም ሥራቸው ነበር። እሳቸውም ስለ ትርጉም ስራ ስፅፉ፤ *...የትርጉም ስራ ቀላል መስሎ የሚታያቸው ሰዎች አሉ። በእርግጥም ኢልብ ወለድ የሆኑ ፅሁፎችን ቃል በቃል መተርጎም እስከዚህም የሚከብድ አይደለም። ነገር ግን ጥበብ ነክ የሆኑ ፅሁፎችን እስከነ ውስጣዊ ምንነታቸው መተርጎም በጣም አስቸጋሪና ተፈታታኝ ስራ ነው። ...ተርጓሚው ለወጡ ስራ ደራሲ፤ ለአንባቢያንና ለገዛ ህሊናውም ታማኝ ሆኖ እውነተኛውን ጭብጥ በትክክል መተርጎም ይገባዋል። በግሌ ጥበብ ነክ የሆኑት ስራዎችን መተርጎም የጀመርኩት በእንግሊዝ ኤምባሲ ውስጥ በትርጉም ስራ ለሰባት ዓመታት ያህል ልምድ ካካበትኩ በሁዋላ ነበር* - ብለዋል።

ተርጓሚ ሣህለ ሥላሴ የትርጉም ስራን አስፈላጊነት ሲያብራሩ፤ *...የሌሎችን ህዝቦች ባህል፤ ታሪክ፤ ሥነ ፅሁፍ ወዘተርፈ ለማወቅ ከፈለግን እነዚህ ሁሉ ወደምናውቀው ቋንቋ ተተርጉመው እንዲቀርቡልን ያሻል።...የአንድን አገር ሥነ ፅሁፍ የሚያበለፅገውም የዚያ አገር ደራሲያን ወጥ ድርሰት በማቅረባቸው ብቻ አይደለም። በእርግጥ ወጥ ድርሰት ማቅረብ የማይታለፍ አብይ ጉዳይ ነው። ነገር ግን የዳበረ ሥነ ፅሁፍ ካላቸው አገሮች ወደራስ ቋንቋ ተርጉሞ ማቅረብም የአንድን አገር ሥነ ፅሁፍ በይበልጥ ያዳብረዋል። የእነ*

*ሼክስፒር የድራማ ስራዎች፤ የእነ ቪክቶር ሁጎ ልብ ወለድ ድርሰቶች፤ የእነ ፑሽኪን የግጥም ስብስቦች፤ ወደ አማርኛ ቋንቋ ሳንመልስ ሥነ ፅሁፋችን በተፈለገው መጠን ያድጋል ማለት ዘበት ነው...*ይላሉ።

እነሆ ተርጓሚ ሣህሌ ይህንን እምነታቸውን ተገበሩ። የታለቁ ፈረንሳዊ ደራሲ ቪክቶር ሁጎ <ሌ ሚዘራብል> (መከረኞቹ) ፤ በሥነ ፅሁፍ የ1938 የኖቤል ተሸላሚ የሆነችው አሜሪካዊት ደራሲ ፐርል በክ <ማዘር> (እምዩ) ፤ የደራሲ ሪቻርድ ራይት <ኔቲቭ ሰን> (ያገር ልጅ) እና ሌሎችም ሣህለ ሥላሴ ብርሃነ ማርያም ለኢትዮጵያ ሥነ ፅሁፍ ተደራስያን ያበረከቷቸው ድንቅ የትርጉም ሥራዎች ናቸው...

<u>*ሐ. ሃያሲ፤*</u> ምንም ያህል የተዋጣለት ደራሲም እንኳን ቢሆን ነፍስያው ሁሌም 'አጮልቃ' የምትመለከተውና የምትጠባበቀው ሃያሲን ነው። ሃያሲ - የሥነ ፅሁፍ ጠበቃ፤ የደራሲ ወጌሻ። ሥነ ፅሁፍ በሃያሲ ስትዳበስ ስትዳሰስ፤ ይታወቃል ህመሟ፤ ይገኛል ስብራቷ። እና ደራሲውም በሃያሲው ብእር ይሞረዳል፤ ይታሻል፤ የብእር ወለምታው ይጠገናል እንዲህ እያለም መፃዒ ድርሰቱም ይፈካል...ከሃያሲው ይማራልና።

የሣህሌን ሃያሲ ብዕር ስለቱን እምናየው ለአብነት በፍኖተ ሕይወት ውስጥ ተዳብለው የቀረቡትን ሂሳዊ ስራዎች ስናነባቸው ነው። እርግጥ ነው ሣህለ ሥላሴ በበርካታ ስራዎች ላይ በጋዜጦችና በመፅሄቶች ያስነበቡዋቸው የሂስ ፅሁፎች ይገኛሉ። በፍኖተ ህይወት ከቀረቡት መኻል ለምሳሌ በሀዲስ ዓለማየሁ <ፍቅር እስከ መቃብር> ላይ ያቀረቡት ትንተና ስናነብ የደራሲና ሃያሲውን የሥነ ፅሁፍ ምዘና ጥልቀት እንረዳለን። በቅኝታቸው ሲያሰፍሩ፤ *...ታላላቅ ደራሲያን የሚፈጥሯቸው ገፀ ባህርዮች በህይወት እንዳሉ ሰዎች ምን ጊዜም ሳይረሱ ይኖራሉ። በኔ አስተያየት ጉዱ ካሳና ፊታውራሪ መሸሻ በመፃህፍት ዓለም ዘላቂነት ካላቸው ከነራስኮሊኒኮቭ፣ ከነ ዡሊያን ሶሬል የሚነፃፀሩ ታላላቅ ባህርዮች ናቸው።* ብለዋል።

ከፍቅር እስከ መቃብር ሌላ - በብርጋዴር ጄኔራል ተስፋዬ ሀብተ ማርያም <የጦር ሜዳ ውሎ>፤ በዓለማየሁ ገላጋይ <አጥቢያ>፤ በተክለ ሃዋርያት ተክለ ማርያም <ኦቶ ባዮግራፊ - የህይወቴ ታሪክ> መፃህፍት ላይ ያቀረቡዋቸው የሃያሲ እይታ ፅሁፎች በፍኖተ ሕይወት ተካትተው ይገኛሉና - እንግዲህ አንባቢ ሆይ ከምንጩ ወርደህ ትኮመኩም ዘንድ ተጋብዘኻል።

ሣህሌ ሃያሲ ናቸው ብንልም ግና እሳቸው ሃያሲ ከመሆናቸው በፊት በሳቸው ጅምር ድርሰቶች ላይ ሌሎች ሃያስያን ያወረዱትን ሂስም በፍኖተ ሕይወት ትርክት ውስጥ አካትተውልን እናገኛለን። ለምሳሌ በ1959 ዓ/ም ያሳተሙት <ወጣት ይፍረደው> የሚለው የመጀመሪያው የአማርኛ ልብ ወለድ ድርሰታቸው በሃያስያን ብእር ከመተቸቱም ባሻገር ራሳቸውም "ያልተዋጣለት ድርሰት' መሆኑን ሲያነጥቡ - *...ምንም እንኳን መፅሀፉ የተዋጣለት ባይሆንም ድክመቴ ምን ላይ እንደሆነ ከዚህ ፅሁፍ ለመረዳት ቻያለሁ።* ***የንግግር ቋንቋና የድርሰት ቋንቋ ለየቅላቸው መሆናቸውን የተረዳሁትና አማርኛዬንም ለማሻሻል ቁርጥ ሀሳብ ያደረግሁት ከዚያ ወዲህ ሆነ...*** *እስከዚያን ጊዜ ድረስ የእንግሊዝኛና በመጠኑም የፈረንሳይኛ መፃህፍት እንጂ አማርኛ መፃህፍትን ማንበብ አላዘወትርም ነበር። ድክመቴን ከተረዳሁ በሁዋላ ግን ያገኘሁትን ሁሉ አማርኛ መፃህፍት አነብ ጀመር፤ ልብ ወለድም ሆነ ኢልብ ወለድ...*በማለት አስፍረዋል።

ይህ 'በንግግር ቋንቋ' በመፃፍና 'በሥነ ፅሁፍ ቋንቋ' በመፃፍ መካከል ያለውን ገደል ክፍተት ቅልብጭ አድርጎ ያሳያል። ሀሳብን በፅሁፍ ማስፈር ስለተቻለ ብቻ "ደራሲ" ወይም "የሥነ ፅሁፍ" ሰው ሊያስደርግ ወይም ሊያሰኝ አይችልምና። ሀሳብን መፃፍ መቻልና ሀሳብን በሥነ ፅሁፍ መፃፍ ከቶም ለየቅል ናቸውና! ለዚህም ነው በድርሰት ዓለም የንግግር ቋንቋንና የሥነ ፅሁፍ ቋንቋን ካለመገንዘብ በሚመነጭ ብዥታ ጥቂት የማይባሉ ጀማሪ ፀሀፍት መፅሀፍ ጠርዘው ማውጣታቸውን እንጂ አቅርቦታቸው 'የንግግር ፅሁፍ" ወይስ 'ሥነ ፅሁፍ" ለመሆኑ ብዙም አስተውሎት የሌላቸው። ከዚህም በላይ ሁሉም ባይሆኑም እንኳ አብዛኞቹ ይህንን ህፀፃቸውን የሚያመለክቱ ሃያስያንን "የብእር ገዳይ" አድርገው ይመለከታሉ።

በአማርኛ የመጀመሪያ ልብ ወለድ ስራቸው ድክመታቸውን የተገነዘቡት ሣህሌ ወደ ሌላ ልብ ወለድ ስራ ከማቅናታቸው በፊት የተሰማሩት ወደ ጥልቅ ንባብ ነበር። ደራሲ ለመሆን ብእር የሚያነሳ ፀሀፊ ሁሉ ንባብ/ ያላቋረጠ የእድሜ ልክ ንባብ፤ የድርሰት አድባር ከምትጠይቀው ምስ አንዱና ዋናው ነውና። የድርሰት አድባር የምትጠይቀው የንባብ ግብር ግን 'ጎጆ ወጪውን' አዲስ ደራሲ ብቻ ሳይሆን የአምባውን ነባር ነዋሪ አንጋፋውንም ደራሲ ጭምር ነው፤ የግብሩ ልክ በሁለቱ መኻል ሊለያይ ቢችልም ቅሉ።

በአማርና ቋንቋ ካቀረቡዋቸው የድርሰት ስራዎች በተጨማሪ በእንግሊዝኛም በርከት ያሉ መፃህፍትን ያበረከቱት ሣህሌ በባእዱ ቋንቋ ቀዳሚ ስራቸው ላይም የሃያስያን ብእር ተመዞባቸው ነበር። እንዲህ ይላሉ፤ *...እኔ በበኩሌ ስለ አፃፃፍ ቴክኒክ በጥልቀት ማንበብና መረዳት የጀመርኩት <ዚ አፈርሳታ> በተባለው መፅሀፌ ብዙ አይነት አስተያየቶችና ትችቶች ከተሰነዘሩ በሁዋላ ነበር። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ስለ አፃፃፍ ቴክኒክና ስለ ትችት ራሱ (ሂስ) በእንግሊዝኛ የተፃፉ መፃህፍትን ገዝቼ አንብቤያለሁ...*በማለት አንጥበዋል።

እነሆ ከእስካሁኑ ትርክት እንደምንረዳው ደራሲ - በድርሰት ዓለም በድርሰት አምባ ኖሮ ለመውለድ፤ የውስጠቱ ክፋይ ዘረ ቃል ውልደቱም ብሩክ ለመሆን...ፍዳው የትየለሌ፤ ማሳውም አታካች፤ ድካሙም የእድሜ ልክ...እንደሆን ያሳየናል። ከድርሰት አምባ የሚወርዱ ብዙዎች፤ በአምባው የሚኖሩ ግን ጥቂቶች ናቸውና!

## 2.2 ፍኖተ ሕይወትና ፖለቲካ

በሶስት ሥርዐተ ማህበሮች (በዘውዳዊ፤ ወታደራዊና ኢህአዴጋዊ) ውስጥ ማለፋቸውን የገለፁት ሣህለ ሥላሴ በየሥርዐተ መንግሥታቱ የተገነዘቡትን ፖለቲካዊ ድባቦች ከተዛማጅ ሰበዞች ጋር በማቆራኘት ተገቢ በሆነ ደረጃ በፍኖተ ሕይወት አካትተዋል። የዐፄ ሃይለ ሥላሴንና የኮሎኔል መንግሥቱን ዘመነ መንግሥታት ምልከታቸውን ለመፅሀፉ አንባቢ ትቼ በወቅቱ በሚገኘው መንግሥት በኢህአዴግ ፖለቲካ ባቀረቡት ምልከታ ላይ እወሰናለሁ።

ሣህሌ ኢትዮጵያ ሀገራቸው ያለ ባህር በር መቀርቀቧ ያንገበገባቸው መሆኑን የምንገነዘበው በመፅሀፉ ውስጥ ካስቀመጡዋቸው የየሥርዐተ መንግሥታቱ ፖለቲካዊ ግምጋሜያቸው አንፃር በአሰብ ጉዳይ ያወረዱት የታሪክ ሀቅ የአቀራረቡ ጥንካሬና አፅንኦት ዘልቆ ሲሰማን ነው። ለዚህ ቅኝት የነቀስኩትን ያለ አንዳች ተጨማሪ ትንታኔ እነሆ አቀርባለሁ፤

*...ለኤርትራ ህዝብ የተሰጠው ምርጫ "ነፃነት ትፈልጋለህ ወይስ ባርነት" የሚል ነበር። ኤርትራውያን ኩሩ ኢትዮጵያውያን እንጂ የማንም ባርያ አልነበሩም። እንዲያውም ለስድሳ ዓመታት ያህል በባእድ አስተዳደር ቆይተው ወደ ኢትዮጵያ ሲመለሱ የኢትዮጵያ መንግሥት ለእነሱ ትኩረት በመስጠት እንደ በኩር ልጅ ነበር የሚንከባከባቸው። ለምሳሌ በጣሊያን አገዛዝ ዘመን ከአራተኛ ክፍል በላይ ትምህርት አይሰጣቸው የነበሩት ኤርትራውያን ከኢትዮጵያ ጋር ከተቀላቀሉ በሁዋላ ግን የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ከመስፋፋቱም በላይ የአስመራ ዩኒቨርሲቲ እንደተከፈተላቸው መርሳት ባልተገባቸውም ነበር። ስለሆነም "ነፃነት" ትፈልጋለህ ወይስ "ባርነት" የሚል ጥያቄ ማቅረብ ከስረ መሰረቱ የተዛባ ነበር።*

*ለኤርትራ ህዝብ የቀረበው ምርጫ የተሳሳተ ከመሆኑም በላይ የኢትዮጵያን ሁኔታ ፈፅሞ ያላገናዘበ ነበር። የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን ስትቀላቀል የወደብን ጉዳይ ሳያነሳ የቀረው ሁለቱ አንድ አገር ከሆኑ ኢትዮጵያ የወደብ ችግር እንደማይኖርባት ያውቅ ስለነበር ነው።*

*ይህ ሳይሆን ቀርቶ ኤርትራ ራሷን የቻለች አገር ትሁን ቢል ኖሮ ግን አሰብን ለኢትዮጵያ ይሰጥ እንደነበር በጊዜው የተደረጉት ድርድሮች ይጠቁማሉ። ኤርትራ ራሷን የቻለች አገር እንድትሆን በትክክለኛው መንገድ በፌዴሬሽንም የሚወሰን ቢሆን ኖሮ የአሰብ ጉዳይ ሳይነሳ ሊቀር ባልቻለም ነበር። አሰብ የአፋር ግዛት በመሆኑ፤ የአፋር ህዝብም በኢትዮጵያዊነቱ ፍፁም የሚያምንና የሚኮራ ህዝብ በመሆኑ፤ እንዲሁም ከዓለም ዐቀፍ እይታ አንፃር ኢትዮጵያ መውጫ መግቢያ የባህር በር ስለሚያስፈልጋት ነው።*

*በጣም የሚገርመው ደሞ የህወሃት/ኢህአዴግ መንግሥት የኢትዮጵያን ህዝብ ሳያማክር የኢትዮጵያን ወደብ፤ አሰብን በገዛ ፈቃዱ ነፃ ወጣች ለተባለችው ኤርትራ እንደ ገፀ በረከት አስረክቦ ሲያበቃ አንዴ ጅቡቲን፤ አንዴ ኬንያን፤ አንዴ ሱዳንን፤ በሌላ ጊዜ ደግሞ ሶማሊያን እየተለማመጠ ወደብ ለመከራየት መኳተኑ ነው። "መሯሯጥ ቢያምርህ ዶሮህን በቆቅ ለውጣት" የተባለው ለዚህ  አይነቱ ሁኔታም አይደል! የህወሃት/ኢህአዴግ አመራር አባሎች  ለኢትዮጵያ አገራዊ ጥቅም መከራከር ሲገባቸው የሌላውን ጥቅም ለማስጠበቅ ጥብቅና የቆሙ እስኪመስል ድረስ ኢትዮጵያ አሰብ የኔ ግዛት ነው ብላ ለመከራከር ህጋዊ መሰረት የላትም ሲሉ ተደምጠዋል። ጉዳዩ የዓለም ዐቀፍ ህግ አዋቂዎችን የሚመለከት ነው። ከዚህም በተጨማሪ መታየት ያለበት ህጋዊ መሰረቱ ብቻ አይደለም። የህዝቦች ትስስር፤ የኢኮኖሚ ግንኙነትና የታሪክና የባህል ዝምድና፤ በተለይ ደሞ ዘላቂ የሆነ የአካባቢ ሠላም እነዚህ ሁሉ መታየት ነበረባቸው....*በማለት አስፍረዋል። (ሰረዝ የቅኝቱ አቅራቢ)

## *መቋጫ*

በ289 ገፆችና በተጓዳኝ ፎቶግራፈፎች የተዋቀረው ፍኖተ ሕይወት በ2000 ዓ/ም ወይም በአዲሱ ሚለኒየም መባቻ መታተሙ የደራሲ ሣህለ ሥላሴ የህይወት ጉዞ የደረሰበትን አንዳች ግዙፍ ምእራፍ አመልካች ሆኖ ይገኛል።

ፍኖተ ሕይወት ትርክተ ፍሰቱ አንባቢን በሥነ ፅሁፍ ሮኬት እያጦዘ ደግሞም አንደርድሮ እያወረደ በስሜት የሚያንገላታ አይደለም። ይልቁንም በዝምታ፤ እንደው በፀጥታ መፍሰሱ ሳይታወቅ እንደሚወርድ ሰፊ ያገር ወንዝ በዘመን ታንኳ እያንሳፈፈ፤ ዘመንን እያስቀዘፈ የሚያነጉድ እንጂ! የአተራረክ ሀቁ፤ ግለ ገድል ያልዞረበት፤ ያልዋለበት። ቃላት ያልተንኳኩበት፤ ያልመከኑበት። ቀመረ ቋንቋው ለሁሉ ተስማሚና ግልፅ። ባህርያት፤ ክስተቶችና አካባቢያዊ ገለጣዎች ምናባዊና ስዕላዊ።

በፍኖተ ሕይወት አንባቢ፤ በሲስ መንደር በቤተ ጉራጌ ከደራሲው ጋር ተወልዶ፤ ዳዳ አናንቃን ተዋውቆ አክብሮና አድንቆ፤ በእመት ኟሪሰብ ክትፎ ጉሮሮረው ተንቋርሮ፤ አባባ ባሪቅየ ( አባባ ሽሜ) በድዳቸው ሲስቁ አብሮ ተንከትክቶ ስቆ፤ በአባ ፍራንሷ ኮርቶ፤...ዘመን አልፎ ዘመን ሲተካ ከሣህሌ ጋር አድጎ ተዳብሎም ኖሮ፤ ከልጅነት እስከ እውቀት የሣህሌ አብሮ አደግ ሆኖ ቁጭ!

ደራሲና ተርጓሚ ሣህለ ሥላሴ ብርሃነ ማርያም ፍኖተ ሕይወትን ስላቋደሱን፤ ትውስታቸውን ስላዋዩን - መቼም ቃላት የልባችንን ከገለጡልን፤ ውስጣችንን ካጋለጡልን - የኢትዮጵያ አምላክ ባሉበት ይጠብቅልን! ሰው በህይወት ዘመኑ፤ እንደ ችሎታው እንዳቅሙ፤ ለሀገር ለወገኑ መልካም ቅርስ ካኖረ ተግባሩ፤ ከኖረበት ትውልድ ባሻገር በተቀጣጣይ ትውልድ ሁሉ፤ ሲዘከር ይኖራል ስሙ፤ አስተማሪ ተምሳሌ ምግባሩ። እነሆም ደራሲ፤ ተርጓሚና ሃያሲ ሣህለ ሥላሴ ብርሃነ ማርያም አንዱ ናቸው!!

በያለንበት ቸር ይግጠመን!

ታህሳስ 2006 ዓ/ም
ጃንዋሪ 2014
ሲድኒ አውስትራሊያ

ስለቅኝቱ አስተያየት ቢኖርዎ፤ የመልዕክት አድራሻዬ ይኸውልዎ፤ mmtessema@gmail.com